ማውጫ


የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ ....... 7

የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥልጣን እና ተግባራት ....... 7

የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description) ....... 9

የኦዲቱ ዓላማ :- ....... 11

የኦዲት አካባቢ ....... 11

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡- ....... 11

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፡- ....... 12

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ :- ....... 13

ክፍል ሁለት ....... 14

የኦዲቱ ግኝቶች ....... 14

ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት በሚውሉ እና ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ ጥራታቸውን ለማሻሻል አስፈላጊው ምርምር መካሄዱን በተመለከተ፡- ....... 14

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከተለያዩ የምርምር ሥራ ከሚሰሩ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡- ....... 16

በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ ማዕከላት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፡- ....... 18

በአርብቶ አደርና እርጥበት አጠር አከባቢዎች በእንስሳት ሃብት ልማት እና ምግብ አመራረትን ማሻሻል በተመለከተ፣ ....... 20

በማዕከላቱ የግብይት ትስስርን ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት የተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ፡- ....... 21

ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን በልዩ ልዩ ብሂር ብሂረሰቦች ቋንቋ ማስተዋወቅን በተመለከተ፡- ....... 23

የፀረ ተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢው የሚፈጥሩትን ተፅእኖ ለመቀነስ የሚጠኑ ጥናቶችን በተመለከተ፤ ....... 25

በኢንስቲትዩቱ ከግብርና ምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎችን በዕቅድ ማካሄዱን በተመለከተ፡- ....... 26

በኢንስቲትዩቱ የልቀት(Center Of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Centers) ማዕከላት በጥናት የተመረጡ መሆኑን በተመለከተ፡- 27

በግብርና መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮች በአጭር ጊዜ ወደተግባር ሊሸጋገሩ የሚችሉ መሆኑን በተመለከተ፡- 29

በግብርና ምርምር የሚቀርቡ ቴክኖሎጂዎች መነሻ ሃሳብ አመራረጥን በተመለከተ፡- 31

በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የሚውል ቴክኖሎጂ የቀረበ መሆኑን በተመለከተ፡- 33

ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ቴክኖሎጂ በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት ፍተሻ መደረጉን በተመለከተ፡-34

ፕሮጀክቶች፣ ግንባታዎች እና የምርምር ተግባራት በታቀደላቸው በጀት እና ጊዜ የተጠናቀቁ መሆኑን በተመለከተ፡- 35

በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ ወይም የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች ማስረጃዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆናቸውን በተመለከተ፡- 39

ኢንስቲትዩቱ በግብርና ምርምር ማዕከላት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡-40

በኢንስቲትዩቱ የመደበኛና ካፒታል በጀት ተመድቦላቸው የግብርና ምርምር የሚያከናውኑ አካላት ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ሥርዓትን መኖሩን በተመለከተ፡- 43

በግብርና ምርምር ማዕከላት በምርምር ሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል በጥናት ላይ ተመስርቶ የተመደበ መሆኑን በተመለከተ፡- 45

በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ግዥዎች የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ መፈፀማቸውን በተመለከተ፡- 47

በኢንስቲትዩቱ የተገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀም እና አወጋገድን በተመለከተ፡- 48

በኢንስቲትዩቱ ስር የሚገኙ ማዕከላት ከ2004- 2006 ዓ.ም ኦዲት የተከናወነ ስለመሆኑ፡- 52

የዘር እና ተረፈ ምርት ሽያጭ ውጤታማነትን በተመለከተ፡- 53

የመደምደሚያ ሃሳቦች 56

ክፍል አራት 69

የማሻሻያ ሃሳቦች 69

አባሪ- 1 74

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 74

አባሪ 2 82

በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አከባቢዎች ዝርዝር ማሳያ፡- 82

አባሪ 3 .......... 84

አባሪ-4 .......... 85

በኢንስቲትዩቱ በጅት ተመድቦላቸው የምርምር ተግባራትን ሲያከናውኑ የቆዩ ተቋማት ከ1999 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም ያልተወራረዱት ገንዘብ ማሳያ ሰንጠረዥ፡- .......... 85

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በኢትዩጵያ እርሻ ሀብት ማስፋፋት ለአገሪቷ ጠቅላላ የኢኮኖሚ እድገትና ለኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ ኑሮ አስፈላጊ በመሆኑ፤ የእርሻ የከብት እርባታና የደን ልማት ዓይነትንና ብዛትን ለማሻሻልና ለማደራጀት የሚቻልበት ደንበኛ መንገድ በማስፈለጉ የእርሻ ሀብት ለማስፋፋት እንዲቻል የጠለቀ (የሳይንስ) ምርምር መቀስቀስና ከምርምሩ የተገኘውን ዕውቀት በሥራ ላይ የሚውልበትን፤ ተዋህዶ ፕላን፤ ፕሮግራምና ዘዴ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ እርሻ ምርምር ኢንስቲትዩት በትዕዛዝ ቁጥር 42/1958 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት እራሱን የቻለ እንስቲትዩት ሆኖ ተቋቋመ፡፡ ከዚያም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማትና ለሕዝቦቿ ማህበራዊ ዕድገት መሰረት የሆነውን ግብርናን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያገለግሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ፣ አገር በቀል የሆኑትን ለማበልጸግና ከውጭ የተገኙትን ከአገሪቱ የግብርና ልማት ፍላጎት ጋር ለማጣጣም ምርምር ወሳኝነት ያለው የልማት እንቅስቃሴ በመሆኑ፣ ምርምር ለአገሪቱ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነት በቀጣይነት ማደግ አስተዋጽኦ የሚኖረው በአንድ ወጥ ሥርዓትና በቅንጅት ሲራመድ ሆኖ በመገኘቱ እና በአጠቃላይ የአገሪቱን ወቅታዊና ዘላቂ የግብርና ልማት ፍላጎት በውጤታማ ምርምር ለማሟላት የሚያግዙ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ፣ የማበልጸግና የማላመድ፣ የማስተባበር፣ የመደገፍና የማበረታታት ተልዕኮ ያለው ድርጅት በማስፈለጉ በ1989 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 79/1989 የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት ተብሎ ተሰየመ፡፡ የድርጅቱም ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን በ1996 ዓ.ም የድርጅቱ ተጠሪነት ወደ ግብርናና ገጠር ልማት ሚ/ር በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 382/96 ዓ.ም እንዲዛወር ተደርጓል፡፡ በ1998 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 471/98 የአስፈጻሚ

መ/ቤቶች ስያሜና የኃላፊነት መጠርያ ለውጥ ሲደረግ እንደገና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተብሎ ተሰየመ፡፡

2. ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሰረት የሆነና ለብሄራዊ የሶሾ- ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ቢሆንም፣ የአገሪቱ ልዩ ልዩ የግብርና ተግባሮች የሚካሄዱት በአብዛኛው በባህላዊ ቴክኖሎጂ ዘዴዎችና መሳሪዎች ነው፡፡ እነዚህ ባህላዊ ዘዴዎችና የምርት መሳሪዎች የአገሪቱ ቁጥር አነስተኛ በነበረበት የምርቱም ፍላጎት መጠነኛ በሆነበትና የተፈጥሮ ሀብትም ሚዛን ከአሁኑ በተሻለ ሁኔታ በነበረበት ዘመን አጥጋቢ ነበሩ ለማለት ይቻል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አብዛኛው የኢትዮጵያ አርሶ አደር የሚጠቀምበት ባህላዊ የግብርና ቴክኖሎጂና መሳሪያ የሚያስገኘው ምርትና ምርታማነት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ እያደገ የመጣውን የህዝብ ቁጥርና ፍላጎት የሚያሟላ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያለው የአሰራር ዘዴ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀምና ለማልማት የሚያስችል አልነበረም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ከአስከተሉት አጠቃላይ ችግሮች መካከል በቂ የምግብ አቅርቦት አለመኖር፣ ለኢንዱስትሪ በጥሬ እቃነት የሚፈለጉ ምርቶችንና የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት የሚያስችሉንን የግብርና ምርቶችን በአይነት በመጠንና በጥራት ለማቅረብ አለመቻል የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3. አገሪቱ ከፍተኛ የእንስሳትና የአሳ ሀብት ያላት ቢሆንም በተፈጥሮ ዝርያ ባህሪያት አለመሻሻል፣ በበሽታ መጠቃትና በአያያዝ ጉድለት ምክንያት ከዚህ ንኡስ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚገኘው ምርትና ምርታማነት ዝቅተኛ ነው፡፡

4. በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በኩልም የአፈር መከላትና የለም መሬቶች መራቆትን፣ የደን ሀብት መሚጠጥንና የዱር አራዊት መመናመን፣ በአገሪቱ የሚገኘውን የገፅና ከርሰ ምድር የውሀ ሀብት በትክክልና በሰፊው በመስኖ የልማት ተግባር ለማዋል ከግብርና ልማት የሚጠበቀውን አስተዋጽኦ እንዳያበረክት አድርጓል፡፡በቆላማ አከባቢዎች የሚገኘውን ሰፊ መሬት በቀላሉ ለማልማት ባለመቻሉ በደጋውና በወይና ደጋው አከባቢ የእርሻ መሬት ጥበት ይታያል፡፡ በአጠቃላይ አገሪቱ ያላትን ከፍተኛ የህዝብ ኃይልና የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ የመጠቀምና ምርታማነቱን ከፍ ለማድረግ አለመቻል ዘርፉ እንደዋንኛው ድክመት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል፡፡

5. ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለማስወገድና በተለይም በምግብ አቅርቦት እራስን ለመቻል፣ መተኪያ የሌለውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና ለማልማት፣ እንዲሁም ኢኮኖሚውን ለመገንባት ለሚደረገው ብሄራዊ ጥረት አስፈላጊውን የጥሪት ክምችትና የውጭ ምንዛሪ ግኝት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ስለሚጠበቅ ባህላዊውን የግብርና ዘዴ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችና ዘዴዎችን ማሻሻልና ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ተስማሚ የሆኑ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ለማግኘትና ለማሰራጨት አግባብነት ያላቸውን የግብርና ምርምሮችንና ስርፀቶችን ማካሄድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡
6. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርናውን ክፍለ-ኢኮኖሚ ከ14.9 በመቶ በላይ ለማሳደግ የተቀመጠውን የአምስት ዓመት (2003- 2007 ዓ.ም) የእድገትና ትራንስፎርሜሽን (Growth and Transformation) ዕቅድ ለማሳካት የሚያስችሉ አዋጭና ውጤታማ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ የሚያስችል ዕቅድ በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
7. ኢንስቲትዩቱ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በቀጣይነት የዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ ለማድረግ በተለይም በሰብል፣ በእንስሳት እና በተፈጥሮ ሀብት ዘርፎች ቅድሚያ በተሰጣቸው የልማት ማነቆዎች ላይ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማካሄድ የአገሪቱን የግብርና ምርቶች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ በሚያደርጉ የአርሶ አደሩን፣ የአርብቶ አደሩንና የከፊል አርብቶ አደሩን የምግብ ዋስትና በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግና ኑሮውን ለማሻሻል በሚያስችሉ እንዲሁም ለዘላቂ ልማት የተፈጥሮ ሃብትን ለመንከባከብና ለማበልጸግ አስተዋጽኦ ያላቸውን ተስማሚና አዋጭ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ አስገብቶ በማላመድና በምርምር በማውጣት በሁሉም የልማት ፀጋዎች ለተጠቃሚዎች ማቅረብን ትኩረት አድርጎ ይሰራል፡፡
8. በመሆኑም የሃገራችንን የግብርና ልማት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችሉ ውጤታማ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን፣ የአሰራርና የአመራረት ዘዴዎችን ለማቅረብና ለማሳደግ ኢንስቲትዩቱ የምርምር ሥራዎቹን በአምስት አበይት የምርምር ዘርፎችና ሦስት ማስተባበሪያዎች በማደራጀትና በስሩ በሚገኙ 25 የምርምር ኬዝ ቲሞች አማካይነት ዕቅዶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ሲሆን በቀጣይ የሁለት ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን ውስጥ የተለያዩ ውጤታማ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚው በማቅረብና በማስፋት ስትራቴጂ

መሰረት በሁሉም አርሶ አደሮች ደረጃ የግብርናን ምርትና ምርታማነት አሁን ካለበት ደረጃ በእቅድ ዘመኑ ማጠናቀቂያ ቢያንስ በሁለት እጥፍ ለማሳደግ ያለመ ነው፡፡ የምርምር ሥራዎች የሚከናወኑት በኢንስቲትዩቱ ሥር ባሉ 17 የፌዴራል የምርምር ማዕከላትና ከኢንስቲትዩቱ ጋር በመተባበር በሚሰሩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የክልል ግብርና ተቋማት፣ በክልል ግብርና ቢሮ ባሉ የክልል ቀጠና የእንስሳት ጤና ላብራቶሪዎች ጋር በመተባበር ነው፡፡

## የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ

| የተመደበ ካፒታልና መደበኛ በጀት በብር | | | አፈጻጸም በብር | | | አፈጻጸም በመቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2004 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | 2004 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | 2004 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም |
| 252,606,061.12 | 294,479,060 | 324,622,450 | 244,881,996 | 290,521,041 | 320,049,008 | 96.94 % | 98.66 % | 99 % |

9. የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ ከመንግሥት የሚመደብ የካፒታል እና የመደበኛ በጀት ሲሆን በሥራ ላይ የዋለው ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፤

## የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥልጣን እና ተግባራት

10. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የተቋቋመበትን ዓላማ እና ራዕይ ለማሳካት የሚያስችሉ ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡፡ እነርሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. በአገሪቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲዎች መሰረት የግብርና የምርምር ስትራቴጂ መንደፍና ቅደም ተከተል መወሰን፣ የሥራ ፕሮግራምና ዕቅድ ማውጣት፣ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም በሚመለከታቸው ክፍሎች ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፤

2. የግብርና ምርምር ፖሊሲ አፈጻጸምን መከታተል፣ አዳዲስና የማሻሻያ የፖሊሲ ሃሳብ ማመንጨት፣ ለመንግሥት ማቅረብ፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ማድረግ፣ ተግባራዊነቱን መከታተል፣
3. በግብርና ምርምር ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት የግብርና ምርምር ማከናወን ወይም እንዲከናወን ማድረግ፣
4. ማንኛውም በድርጅቱ ስር የሚተዳደር የግብርና ምርምር ማዕከል እንደገና እንዲደራጅና እንዲታጠፍ፣ አዲስ ማዕከላት እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ሥነ ምህዳሮች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣
5. ጠቀሜታቸው የተረጋገጠ የግብርና ምርምር ውጤቶች ተጠቃሚው ክፍል እንዲያውቃቸው በሥራ ላይ እንዲውሉ በፌዴራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ውጤታማ ቅንጅት እንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት መዘርጋት፣ ተግባራዊ ማድረግ፣ ተግባራዊነቱን መከታተል፣
6. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ ለማስፋፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ አመቺ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በልዩ ልዩ የብሔር/ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የአህዝቦት/ማስተዋወቅ/ ተግባር ማከናወን፣
7. በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱና የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማከማቸትና ማሰራጨት፣ የመረጃ ቅብብል ሥርዓት መገንባትና መምራት፣
8. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በግብርና ትምህርት፣ ምርምርና ሥርዓት እንዲሁም ምርት እንቅስቃሴ የእርስ በርስ መደጋገፍ እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
9. በግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና ያለውንም የሰው ኃይል ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ፣ በድርጅቱ የተሰማራውን የሰው ኃይል አቅም ማሳደግና መገንባት የሚያስችል መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፣
10. የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚደራጁበትንና የሚጎለብቱበትን ማመቻቸት፣ መርዳትና ማበረታታት፤

11. የግብርና ምርምርን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳይ ላይ መሳተፍና መንግሥትን ማማከር፤
12. አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ከአለም አቀፍና አህጉራዊ የግብርና ምርምር ተቋማትና ድጋፍ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ አላማ ካላቸው ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መመስረት፣ ትብብር ማድረግ፣ ስምምነቶችን መፈራረም፣ ተግባራዊ ማድረግ ወይም ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤
13. ለክልል የግብርና የምርምር ማዕከላት ተገቢውን የመረጃ አገልግሎት መስጠት፣ ጥያቄም ሲቀርብ አቅሙ በፈቀደ መጠን የቴክኒክ ድጋፍና እገዛ ማድረግ፤
14. በፌዴራልና በክልል የምርምር ማዕከላት በሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽና የሀብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክት ግምገማ ሥርዓት አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መዘርጋት፤
15. በግብርና ምርምር ላይ የተሰማራ ወይም የሚሰማራ ማንኛውንም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን መያዝ፤
16. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማች ተግባሮችን ማከናወን፤

## የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description)

11. የምርምር መነሻዎች ሃገራዊ የምርምር ስትራቴጂ እና ወቅታዊ አንገብጋቢ ችግሮች (Emerging Issues) ሲሆኑ፣ ይህም የሥራ ሂደት ባለቤቱ ወሳኝ ባለድርሻዎችን በመለየት እንዲወከሉ በማድረግ ባለድርሻዎች፣ ተመራማሪዎችና የሥራ ሂደት ባለቤት በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የልማት ችግሮችን፣ ክፍተቶችንና የምርምር የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በጋራ በመለየትና ቅደም ተከተል በማስያዝ ቀዳሚ የምርምር የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንዲቀመጡ ይደረጋሉ፡፡

የተለየና ቀዳሚ የምርምር የመፍትሄ አቅጣጫን መነሻ በማድረግ የሥራ ሂደት ባለቤቱ የምርምር ዕቅድ ቡድን (Research Planning Case Team) በመመስረት የምርምር ተግባራት (Research Activities) እንዲቀረጹ፣ የአሰራር ስልት

እንዲነደፉ፣ ተፈላጊ በጀት እና የድርጊት መርሃ-ግብር ዝርዝር እንዲያዘጋጁ በማድረግ የተሟላ የምርምር ፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

የተሟላ የምርምር ፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድ ከተዘጋጀ በኃላ በሥራ ሂደት ባለቤቱ የምርምር ፕሮጀክት ዕቅድ ግምገማ ቡድን (Peer Reviewers) ተለይቶ የምርምር ፕሮጀክት ዕቅዱን በጥልቀት በመገምገም፣ የማዳበሪያ ሃሳብ በመስጠት ተቀባይነቱ የተረጋገጠና የዳበረ የምርምር ፕሮጀክት ሰነድ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

ያለቀለት ቴክኖሎጂ ከውጪ በማስገባት ተስማሚነቱን በመፈተሽ ማላመድ፡-

- ✓ ቴክኖሎጂ ከውጭ በማስገባት ተስማሚነቱን ለመፈተሽ የፀደቀ ፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድን መነሻ በማድረግ ስለቴክኖሎጂው ዝርዝር መረጃ ተሰብስቦ፣ ግንኙነት ተፈጥሮና አስፈላጊው ፎርማሊቲዎች ከተከናወኑ በኋላ የቴክኖሎጂ ማስገባትና ኳራንቲን ፍተሻ ተደርጎ የምርታማነትና የማላመድ ብቃት ግምገማ (የምርት መጠንና ጥራት፣ በሽታን የመቋቋምና ሥነ-ተዋልዶ/የመራባት) በማድረግ ተስማሚነቱ የታወቀን ቴክኖሎጂ በማረጋገጥ፣ በመመዝገብና በመልቀቅ ቴክኖሎጂው ሥራ ላይ እንዲውል ይቀርባል፡፡

ምሉዕ ቴክኖሎጂ ለማፍለቅ የሚያግዝ ሥልታዊ ምርምር፡-

- ✓ ይህ ምርምር የሚያተኩረው የተጠቃሚውን ችግር ለመፍታት መሰረታዊ መረጃ በሚፈልጉና ውጤታቸው ወደ ተግባራዊ ምርምር የሚያመሩ የምርምር ተግባራት ሲሆኑ በተለይ በቤተ ሙከራ ደረጃ የሚተገበሩት ለአፈጻጸማቸው ልዩ ክህሎትና ፋሲሊቲም የሚፈልጉ ናቸው፡፡ የክንውን ሂደቱም ምሉዕ ቴክኖሎጂ ለማቅረብ የሚያግዝ የጸደቀ ምርምር ፕሮጀክት በመነሳት የቅኝት ጥናት ከተደረገ በኋላ በቤተ ሙከራ ግምገማ በማድረግ በመጨረሻም መሰረታዊ መረጃዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

ቴክኖሎጂን ከነሙሉ ፓኬጁ ማፍለቅ፡-

- ✓ ዝርያን ለማሻሻል የፀደቀ ምርምር ፕሮጀክት ዕቅድ ሰነድን መሰረት በማድረግ የተገልጋዩን ህብረተሰብ ያሳተፈ የዝርያ ማሻሻል ትግበራና ስልት በማውጣት ተፈላጊ ዝርያ የሚገኝበትን አከባቢ ቅኝት በማድረግ መስራች የሀገር ውስጥ ዝርያን በምርምር ማዕከል ደረጃ በማራባት መረጣ ከተካሄደ በኋላ አዲስ ዝርያ በማውጣትና በማባዛት ከዚያም የዝርያን ውጤታማነት በማረጋገጥ፣

በመመዝገብ መልቀቅና ማውጣት ነው፡፡ዝርዝር ሥዕላዊ መግለጫው **በአባሪ 3** ቀርቧል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ ፡-

12. የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሚያከናውናቸው የግብርና ምርምሮች ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት የተላበሰና በዘርፉ የወጡትን ህግና ደንቦችን መሠረት ያደረገ ፣ ሥርዓት የተከተለ እና የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በቀጣይነት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ በተለይም በሰብል፣ በእንስሳት እና በተፈጥሮ ሀብት ዘርፎች ቅድሚያ በተሰጣቸው የልማት ማነቆዎች ላይ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማካሄድ የአገሪቱን የግብርና ምርቶች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ በሚያደርጉና ለሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ፣ የአርሶ አደሩን፣ የአርብቶ አደሩንና የከፊል አርብቶ አደሩን የምግብ ዋስትና በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግና ኑሮውን ለማሻሻል በሚያስችሉ እንዲሁም ለዘላቂ ልማት የተፈጥሮ ሃብትን ለመንከባከብና ለማበልጸግ አስተዋጽኦ ያላቸውን ተስማሚና አዋጭ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ አስገብቶ በማላመድና በምርምር በማውጣት በሁሉም የልማት ፀጋዎች ለተጠቃሚዎች ማቅረቡንና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚያግዝ ድጋፍ ለማድረግና በተቋሙ አሰራርም ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ

13. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area) በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል እና የእንስሳት የምርምር ሥርዓት አፈጻጸም ቀልጣፋ፣ኢኮኖሚያዊና ስኬታማ በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን እና ለዚሁ ተግባር የዋለው ግብአት ያስገኘውን ተመጣጣኝ ውጤት (Value for Money) ለማረጋገጥ ነው፡፡

## የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡-

14. በተመረጠው የኦዲት አከባቢ (potential audit area) ሥር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (audit issue) ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም፡

1. የአገሪቱን የግብርና ምርምር ቀልጣፋ፣ የተቀናጀ ውጤታማና በልማት ፍላጎት ላይ ያተኮረ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም አቅም መገንባቱን ማረጋገጥ፤
2. የቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ ብዜትና ሥርጭት በሚፈለገው መጠን፣ ጥራቱን ጠብቆ፣ በአጭር ጊዜና አነስተኛ ወጪ ለተጠቃሚው እንዲቀርብ መደረጉን ማወቅ፤
3. የሃብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችልና የተቋሙን ብቃትና ውጤታማነት የሚያጠናክር ክትትልና ግምገማ እንዲሁም የመረጃ እና የንብረት አያያዝ ሥርዓት በኢንስቲትዩቱ የተዘረጋ መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፡-

15. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 43 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ጥቅምት 1986 ዓ.ም የወጣው ሀገራዊ የግብርና ምርምር ፖሊሲ እና እስትራቴጂ፣ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 79/4989 ዓ.ም፣ በየካቲት 2004 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲ፣ በህዳር 2000 የተካሄዱት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ቢፒአር ጥናቶች የእንስሳት እና የሰብል ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት የሥራ ሂደት ፍሰትና የአተገባበር መመሪያ በህዳር 2000 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለ፣ የገጠር ልማት ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጂዎችና ሥልቶች ህዳር 2002 ዓ.ም፣ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የአምስት አመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2003- 2007 ዓ.ም፣ የኢንስቲትዩቱ ማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤዎች፣ አዲሱ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ሥርዓት ማስተባበሪያ አደረጃጀት ረቂቅ ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር <u>በአባሪ 1</u> ተያይዘዋል፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ፡-**

16. የክዋኔ ኦዲቱ የሸፍነው ከ2004 እስከ 2006 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል እና እንስሳት የምርምር ሥርዓት አፈጻጸምን በሚመለከት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በኢንስቲትዩቱ ሥር በሚገኙ እና በተመረጡ ስምንት (ሆለታ፣ ደብረዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ አሶሳ እና ወረር) ማዕከላት እንዲሁም በናሙና በተመረጡ ሁለት (ባኮ እና ጅጅጋ) የክልል የግብርና ምርምር ማዕከላት እና ሰባት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (አሶሳ፣ አምቦ፣ አዳማ፣ ጅጅጋ ዩነቨርሲቲዎች እንዲሁም አሶሳ፣ ባኮ እና ሆለታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት/ ኮሌጆች) ላይ ሲሆን የምርምር ውጤትን በቅርበት የሚጠቀሙ ሞዴል አርሶ አደሮች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡ ኦዲቱም የተከናወነው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመ/ቤቶቹን የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በቼክ ሊስት በመወያየት እና በማጣራት፣ የግብርና ምርምር ሥርዓትን ለመስፈጸም ሥራ ላይ የዋሉ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስ፣ የምርምር ማዕከላቱንና የሚመለከታቸው ተቋማት አሰራር በአካል ተገኝቶ በመገምገም እና በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ላይም አስፈላጊውን ትንተና (Analysis) በማካሄድ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲቱ ግኝቶች

### ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት በሚውሉ እና ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ ጥራታቸውን ለማሻሻል አስፈላጊው ምርምር መካሄዱን በተመለከተ፡-

17.ለኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት ለሚውሉ እና ወደውጭ ሀገር ገበያ ተልከው የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉ እንዲሁም የምግብ ጠቀሜታቸው ከፍተኛ የሆኑ የግብርና ምርቶችን ጥራታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል አስፈላጊውን ምርምር ሊካሄድ ይገባል፡፡

18.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 ማዕከላት (ሆለታ፣ ደብረ ዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ ወረር እና አሶሳ) በ6ቱ(ቁሉምሳ፣ ወረር፣ ሆለታ፣ አምቦ፣ ባኮና አሶሳ) ከአከባቢያቸው ስነ ምህዳር ጋር የሚጣጣሙ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት ሊውሉ የሚችሉ እና የግብርና የወጪ ምርትን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያግዙ የግብርና ምርቶች በተለይ በቅባት እህሎች በጥጥ፣ በሰሊጥ፣ የሰብል ምርቶች በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ እና ከአትክልት የስኳር ድንች እንዲሁም በእንስሳት ዘርፍ የበግና የፍየል ዝርያዎች እና የቆዳና ሌጦ ምርቶችን ጥራት ለማሻሻል የሚያስችል ምርምር በማዕከላቱ በእቅድ ተይዘውና ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው በሚፈለገው ደረጃ የማይከናወኑ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰለሱ መረጃዎች፣ ለማዕከላቱ የሥራ ኃላፊዎች በቀረቡ ቃለ መጠይቆች እና ከተሰጡ መልሶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

19.የቅባት እህሎች ጥራት ማሻሻያ ሙከራ አፈፃፀምን በተመለከተ በመልካሳ፣ በሆለታ፣ በወረር፣ በቁልምሳና በባኮ እና በአምቦ ማዕከላት የተካሄዱት ምርምሮች አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች አተገባበር የአቅም ውስንነት (በሰው ሃይል፣ ፋይናንስና ፋሲሊቲ) እንደነበረበት በኦዲት ወቅት በማዕከላቱ ከተከለሱ ማስረጃዎችና የስራ ኃላፊዎች ከሰጧቸው ማብራሪያዎች ለማወቅ ተችላል፡፡

20.በተመሳሳይ መልኩ የቢራ ገብስን በጥራት ለማምረት የማያስችሉ ችግሮችና ቅድመ ሁኔታዎች መኖራቸው እነሱም ገብሱ በሚበቅልበት ወቅት አብሮ

የሚበቅል የሲናር ችግር መኖር፣ ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተዘሩ ዘሮች ከሌላ ዝርያ ጋር የተቀላቀሉ በመሆናቸው አርሶ አደሮች ያመረቱት የቢራ ገብስ ጥራቱን ያልጠበቀ እንዲሆን በማድረጉ አርሶ አደሮች ካመረቱት ምርት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንዳደረጋቸው በሌሙና በልቢሎ ወረዳ የዳዋ ቡርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር እና በሂጦሳ ወረዳ የኦዳ ጅላ ቀበሌ የሚገኙ ሞዴል አርሶ አደሮች በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለማወቅ ተችላል፡፡

21. እንዲሁም ባቄላ አኩሪ አተር እና አተርን ጥራት ባለው መልኩ ለማምረት የሚያስችሉ የዋግ፣ የትል እና የአረም መድሃኒት ለመጠቀም የሚያስችሉ ጥናቶች እና የምርምር ውጤቶች በምርምር ማዕከላቱ ተከናውነው ለተግባራዊነት ወደ አርሶ አደሩ አለመድረሳቸው በተለይ በባኮ (ሰደን ቂጤ እና ቱሉ ሰንጎታ) እና አሶሳ (ኮሞሻ-28 እና አንባ -14 ) አከባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች አኩሪ አተር አምርተው የተመረተው ምርት የጥራት /የብቅለት/ ችግር ያለበት በመሆኑና ለዚህ ችግር መፍትሄ ባለማግኘታቸው ያለ ውጤት መቅረታቸው ታውቋል፡፡

22. በሌላ መልኩ በግብርና ምርምር ማዕከላቱ በተወሰነ ደረጃ በሚካሄዱ የቫይታሚንና የፕሮቲን ከፍተኛ ይዘት ያላቸውን የበቆሎና የስንዴ ዝርያዎች ውጤትን በግንዛቤ ማነስ ችግር በአግባቡ እንዳልተጠቀሙበት በኦዲት ወቅት በታዩት ማዕከላት አካባቢ የሚኖሩና የምርምር ውጤት በቀዳሚነት ተጠቃሚ ከሆኑ ሞዴል አርሶ አደሮች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. ስለ ሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የምርምር ማዕከላት የተሰጣቸው የምርምር ተልዕኮ ሥነ ምህዳርን መሰረት አድርጎ የተለያየ መሆኑ ለምሳሌ ሰሊጥ በተመለከተ በሁመራ ምርምር ማዕከላት፣ ስኳር ድንች በሃዋሳ ምርምር ማዕከላት የሚካሄዱ ምርምሮች እንጂ የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ አለመሆናቸው፤ ጥራትን በተመለከተ የምርምሩ ዋና ተግባር የምርት ጥራት ማስጠበቅ አለመሆኑን እና ከአርሶ አደሩ የእንክብካቤ እና የግንዛቤ ማነስ ችግር ጭምር የመጣ መሆኑን እንዲሁም ለዚህ ችግር በዋነኛነት የሚመለከተው የግብርና ኤክስቴንሽን መሆኑን፤ የበግና ፍየልን አስመልክቶ ለኤክስፖርት የሚበቁ ዝርያዎች ላይ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት

መኖራቸውን እንዲሁም ቆዳና ሌጦ ላይ ክፍተቱን የሚቀበሉት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

24.የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የግብርና ምርምርን ማከናወን ወይም እንዲከናወን ማድረግ/ማስደረግ ኃላፊነታቸው መሆኑ እና የምርምር ውጤቶች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማስገኘት ያለባቸው ሲሆን የጥራት መጓደል እንዳይኖር መከታተል እና የጥራት ችግር ሲከሰት በችግሩ ላይ ምርምርና ጥናት በማካሄድ እንዲፈታ ማድረግ/ማስደረግ ያለባቸው በመሆኑ የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያዳግተናል፡፡

25.ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት በሚውሉ እና ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ ምርምር ባለመከናወኑ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደሩ ከኢንዱስትሪ እና ከውጭ ገበያ ማግኘት የነበረበትን ጥቅም እንዳያገኝ ያደረገው መሆኑ፤ እንዲሁም ጥራታቸውን ለማሻሻል አስፈላጊው ምርምር ባለመካሄዱ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮቹ ካመረቱ ምርት እንዳይጠቀሙ አድርጓል፡፡

## የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከተለያዩ የምርምር ሥራ ከሚሰሩ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-

26.በፌዴራል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በግብርና ሚ/ር ግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የምርምር ድግግሞሽ (Duplication Of Effort) እንዳይኖር ሊደረግ ይገባል፡፡

27.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት (ሆለታ፣ ደብረ ዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ ወረር እና አሶሳ) በፌዴራል ግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ትስስርና ተግባቢነት ባለመኖሩ ማዕከላቱ በግብርና ጽ/ቤት አስተባባሪነት በተካሄደው የADPLAC /የግብርና

ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል ሰብሰባ ላይ የማይገኙ መሆኑ፣ ከአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ተቋማት(FTC) ጋር በቅርበት የማይሰሩ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

28.በማዕከላቱ የሚከናወኑ የምርምር ውጤቶችን በግብርና ኤክስቴንሽን እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየጊዜው በተከታታይነት የማያሳውቁ መሆኑን፣ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በፌዴራልና ክልል ምርምር ማዕከላት በመሰረታዊ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዙሪያ፣ የማንጎ አመራረትና ድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ፣ የወተት ከብት እርባታ ዘዴ፣ የበግና ፍየል ዕርባታ ሥልጠና፣ የሰሊጥ የተሻሻሉ አሰራሮች፣ በዶሮ እርባታ ላይ የተሰሩ ሥራዎች፤ዘመናዊ የበግና የፍየል ማድለብ ሥራ ሥልጠና እና የማንዋል ዝግጅት፤የእንስሳት መኖ እና አመጋገብ ዘዴ፤ቆዳና ሌጦን በአግባቡ የማምረት እና የመያዝ እንዲሁም ወደ ገበያ ማቅረብ ዘዴ የሥልጠና ማንዋል ዝግጅት፤የተሻሻሉ የንብ እርባታ ዘዴ፤ በስንዴ ዝርያ የማላመድ፣ በበቆሎና በተባይ መከላከል ዙሪያ በተደጋጋሚ/ በተመሳሳይ ወቅት እና ጊዜ ያለቅንጅት/ የተሰሩ/እየተሰሩ ያሉ የምርምር ተግባራት መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት ከማዕከላቱ ፕሮግረስ ሪፖርት፣ ከሪሰርች ዳይሬክሬቶች፣ ዕቅዶች እና ከተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

29.በኦዲቱ በታዩት የግብርና ምርምር ማዕከላት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ማዕከላቱ በቅንጅት ለመስራት ፍላጎት ያላቀረቡ መሆኑ፣ በመዋቅር ደረጃ የሚያስተሳስር አካል ባለመኖሩ፣ የADPLAC/ የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል ሰብሰባ ለማካሄድ በጀት ባለመኖሩ እና አገራዊ/ክልላዊ የምርምር አማካሪ ካውንስል ሥርዓት በመቋረጡ የተጠቀሱት ተቋማት የሚገናኙበት መድረክ ያልተፈጠረ መሆኑን ነገር ግን ይህ ወደፊት መስተካከል ያለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

30.የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከፌዴራል እስከ ወረዳ የሚደርስ የADPLAC አደረጃጀት መኖሩን እና ከበፊቱ በተሻለ መንገድ ቅንጅት ያለ መሆኑን ይሁን እንጂ ወደ ታች ሲወርድ

አልፎ አልፎ የላላ ግንኙነት መስታዋሉን እንዲሁም የምርምር ሥራ ድግግሞሽ ላይ የተሰጠው አስተያየት ትክክል መሆኑን እና ለዚህም የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ካውንስል ተቋቁሞ ሥራዎችን ያቀናጃል ተብሎ የሚጠበቅበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

31.የፌዴራል ግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት ባለመኖሩ የምርምር ስራዎች በተደጋጋሚ የሚከናወኑ መሆኑ፣ ለየዘርፉ የሚመደበውን በጀት በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራ ላይ እንዳይውል ከማድረጉም በላይ ከላይ በተጠቀሱት ተቋማት መካከል የቅንጅታዊ አሰራሩ አለመጠናከሩ በተቋማቱ በተናጠል የሚካሄዱት ምርምር ስራዎች አገራዊ ፋይዳና እሴት በሚጨምር እና የአርሶ አደሩን ውጤታማነት በተሸለ እንዲጎለብት፣ የአሰራሩን ቀጣይነት (Sustainability) እንዲጠናከር እና የተቋማቱን የአሰራር ተጠያቂነት በሚፈጥር መልኩ እንዳይፈፅም አድርጎታል፡፡

## በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ  ማዕከላት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፡-

32.በኢንስቲትዩቱ በሚገኙ በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ያላቸውን ግብዓት እና የሰው ሃይል (scarce resourse) በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል ቅንጅታዊ  አሰራር ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

33.በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ወቅት በታዩ ስምንቱም ማዕከላት በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ለማወቅ ተችላል፡፡ በማዕከላቱ ሥር የሚገኙ የተለያዩ ተመሳሳይ የምርምር ዘርፍ  ላብራቶሪዎች የሚሠሩትን ሥራ አቀናጅተው የማይተገብሩ እና በአንዱ ዘርፍ ያለውን የላብራቶሪ ዕቃ/ኬሚካል ሌላኛው ዘርፍ የማያውቀው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

34.እንዲሁም በመልካሳ ምርምር ማዕከል በ2006 ዓ.ም ቢሾላ አካባቢ የተዘራ ቦሎቄ ከበቀለ በኋላ ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ የደን ምርምር በላዩ ላይ የደን ተክል መትከሉ፣ በሁሉም ማዕከላት በሰብልና በእንሰሳት ዘርፎች በሚካሄዱ ምርምሮች አንዱ ምርምር ለሌላው የምርምር አይነት ግብአት እንዲሆን የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ማለትም የኮምፖስት ሥራ፣ የከብት መኖን ከሌሎች ሰብሎች ጋር በማፈራረቅ፣ ለእንስሳት መኖ በማዋል ውጤታማ ሥራዎች የማይሰሩ መሆኑ፣ በቡድን ሊከናወኑ የሚችሉ የምርምር ስራዎችን በቡድን አለመሰራት ማለትም አንድ ሰራተኛ ሥራ በሚለቅበት ወቅት ሌላው ሰራተኛ የተጀመሩ ተግባራትን ማስቀጠል አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡና ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ባለሞያዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

35. ስለ ሁኔታው የስምንቱም ማዕከላት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ላብራቶሪን በተመለከተ አሁን መደራጀት መጀመሩ፣ አብሮ ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀት ባለመኖሩ እና ሁሉም የስራ ዘርፎች የተለያየ ባህሪ ያላቸው በመሆኑ መቀናጀት አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡ በሌላ መልኩ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ምርምር የቡድን ሥራ እንደሆነና አልፎ አልፎ ሰራተኞች ሲለቁ ማስቀጠል ያልተቻለበት ውስን አጋጣሚዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እና በሰብልና በእንስሳት በቅንጅት የሚሰሩ ሥራዎች በአንድ ወቅት ላይጀመሩ ስለሚችሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

36. በኢንስቲትዩቱ በሚገኙ በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተግባራዊ ባለመደረጉ ማዕከላቱ ያላቸውን ውስን ኃብት በጋራ በመጠቀም ውጤታማ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ በተመሳሳይ ጊዜ የሚከናወኑና እርስ በርስ ሊደጋገፉ የሚችሉ የምርምር ዘርፎች ማለትም የሰብልን ዘርፍ ከእንስሳት ዘርፍ ጋር በማቀናጀት ሊመጡ ይችሉ የነበሩ የምርምር ውጤቶች እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡

### በአርብቶ አደርና እርጥበት አጠር አከባቢዎች በእንስሳት ሃብት ልማት እና ምግብ አመራረትን ማሻሻል በተመለከተ፣

37. በአርብቶ አደርና እርጥበት አጠር አከባቢዎች በእንስሳት ሃብት ልማት፣ በእንስሳት መኖ በማምረትና በማሻሻል ዙሪያ የምርምር ውጤቶች/ቴክኖሎጂዎች/ ሊዘጋጁና ለተጠቃሚው ሊሰራጩ ይገባቸዋል፡፡

38. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች (ወረር፣ ጅጅጋ እና አሶሳ) የእንስሳት ሃብት ልማት፣ የእንስሳት መኖና ምግብ የማምረትና የማሻሻል ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በእነዚህ አካባቢዎች የእንስሳት ዘርፍ ላብራቶሪ እንዲኖር አለመደረጉ፣ የእንስሳት ቴክኖሎጂ ሥርጭቱ ደካማ መሆኑ፣ የተሻሻሉ የወተት ከብት ዝርያዎች አቅርቦት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የሲንክሮናይዜሽን (የኮርማና የጊደር ፍላጎት የማጣጣም ሥራ) ውጤታማ በማድረግ ተጠቃሚው ጋር እንዲደርስ ያልተደረገ ሲሆን በቤንሻንጉል ክልል የእንስሳት እርባታ ስብጥር ወደ 47 በመቶ የሚወክሉት ፍየሎች መሆናቸውን መረጃዎች የሚያመለክቱ ቢሆንም በፍየሎች እና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ምርምር አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በንብ በሽታ እና በዶሮ እርባታ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ አለመደረጉ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ዶክሜንቶች እና የእንስሳት ሃብት ልማት እና ምግብ አመራረት አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ሞዴል አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሮች ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ስለ ጉዳዩ የጅጅጋ፣ ወረር እና አሶሳ ግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የእንስሳት ቴክኖሎጂ መነሻ ካፒታል የሚፈልግና ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆኑን፣ የተሻሻሉ የወተት ከብት ዝርያዎችን ብዜት የሚያካሂድ ባለመኖሩ የእንስሳት ቴክኖሎጂ ሥርጭት ደካማ እንዲሆን ማድረጉን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በአገር ደረጃ የተሻሻሉ የወተት ከብት ዝርያዎችን ለአርሶ አደሩ ለማሰራጨት የተለያዩ የልማት ተቋማት አስተዋጽኦና

የሥራ ትስስር አስፈላጊ በመሆኑና ይህም ተግባራዊ አለመደረጉና፣ ከእንስሳት በሽታ ጋር በተያያዘ ከተመራማሪዎች ፍልስት የተነሳ ምርምሩን በጥልቀት በመስራት ወደ መፍትሄ መምጣት አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጅጅጋና ወረር አከባቢዎች አርብቶ አደሩ ለቴክኖሎጂዎች ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም በአሶሳ የካፒታል ውስንነት መኖሩ እና በክልሉ የገንዲ በሽታ መስፋፋት በመኖሩ ምክንያት በተጠቀሱት አካባቢዎች የእንስሳት ሃብት ልማት እና ምግብ አመራረትን ማሻሻል እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

40. በሌላ መልኩ የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አርብቶ አደሩ አከባቢ ያለው ምርምር ጠንካራ ያልሆነበት ምክንያት ክልሎቹ ለምርምር ትኩረት ባለመስጠታቸው ሲሆን ኢንስቲትዩቱ ግን በዚህ አካባቢ ተግባራቱን ለማጠናከር በዳይሬክቶሬት ደረጃ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደርን ጉዳይ የሚያስፈጽም ክፍል በማቋቋም እያጠናከረ ያለበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩት አካባቢዎች በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች ዙሪያ በዘርፉ የተከናወኑ ተግባራት ዝቅተኛ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. በአርብቶ አደርና እርጥበት አጠር አከባቢዎች በእንስሳት ሃብት ልማት፣ በእንስሳት መኖና በምግብ የማምረትና የማሻሻል ዙሪያ የምርምር ውጤቶች/ቴክኖሎጂዎች እንዲቀርቡ አለመደረጉ በአርብቶና እርጥበት አጠር አከባቢ የመኖ እጥረት እንዲከሰት ማድረጉ ለምሳሌ በመልካ ወረር አከባቢ በሐምሌ እና ነሃሴ አከባቢ የተከሰተውን የመኖ እጥረት እና የእንስሳት ሞት መከሰትን እና በአሶሳ የገንዲ በሽታ እየተስፋፋ ያለበትን ሁኔታ መኖሩ እንዲሁም የእንስሳት ብዜት የሚያከናውን ተቋም ባለመኖሩ  በዚህ አከባቢ የሚኖሩ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች ከቴክኖሎጂው ውጤት ተጠቃሚ እንዳይሆኑና የእንስሳት ሀብታቸውን የምርት ጥራት ደረጃ እንዲያሻሽሉና በተሰማሩበት የግብርና ዘርፍ የተሻለ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

## በማዕከላቱ የግብይት ትስስርን ለመፍጠር  የሚያስችሉ  ተግባራት የተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ፡-

42. በሰብል እና በእንስሳት ዘርፎች የተገኙ የግብርና ውጤቶችን ግብይት ትስስርን ለመፍጠር እና አከባቢውን በይበልጥ ለማልማትና ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ተከናውኖ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

43. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱ ማዕከላት በሰብል እና በእንስሳት ዙሪያ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠርና ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት እንዳልተከናወነ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች እና የግብርና ጽ/ቤት ባለሙያዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

44. በመልካሳ እና ቁሉምሳ የገበያ ትስስር ጥናቱ ባለመከናወኑ ድንች፣ ሽንኩርት እና ቲማቲም በአከባቢው በስፋት የሚመረት ቢሆንም የገቢያ ችግር ያለባቸው መሆኑንና በሆለታ በሰብል ዘርፍ ኑግ እና ተልባ ላይ አርሶ አደሩ ገበያ ላይ አቅርቦ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡ እንዲሁም በእንስሳት ዘርፍ ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኤጀሬ፣ ደንዲ፣ ወልመራ፣ ጀልዱ፣ ጥቁር እንጪኒ፣ አቡሽጊ እና ቀቤና አከባቢ የመኖን ዘር እጥረት ለመቀነስ የተከናወኑ ተግባራት ቢኖሩም የተመረቱ ዘሮችን ለአርሶ አደሮች በመሸጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚያስችላቸው ሁኔታ አለመፈጠሩን ለማወቅ ተችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በወረር በሰብል ዘርፍ ሰሊጥ፣ ስንዴና በቆሎ እንዲሁም በእንስሳት ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የእንስሳት ተዋጽኦን አርብቶ አደሩ/ከፊል አርብቶ አደሩ ተጠቃሚ ሊሆኑ አለመቻላቸውን እንዲሁም በአሶሳ እና ባኮ አከባቢ አኩሪ አተር ለገበያ ቀርቦ ውጤታማ እንዳልሆኑ በአከባቢዎቹ ከሚገኙ ሞዴል አርሶ አደሮች እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

45. የስምንቱም ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በገበያ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተው ባለመስራታቸው ጥናቶችን ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን፣ በአንዳንድ ምርቶች ላይ አርሶ አደሮቹ ትኩረት ሰጥተው በስፋት በማምረታቸው የገበያ ትስስር ባለመኖሩ ችግሮቹ ሊከሰቱ የቻሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሩ በጥራት ሰብሉን ተንከባክቦ ባለመያዙ የገበያ ችግር ሊፈጠር የሚችልበት

ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም በወረር እና አሶሳ ግብርና ምርምር ማዕከላት የገበያ ትስስር ጥናት ያላካሄዱት የአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ የግብርና ውጤቶች ለገበያ እያቀረቡ ያሉት በቅርብ ጊዜ በመሆኑ ህብረተሰቡ ከራሱ አልፎ ለገበያ የሚያቀርበው ሰፊ ምርት ባለመኖሩ ጥናቱ ያልተካሄደ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

46. የኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የግብይት ሥርዓት መፍጠር በዋናነት የምርምር ተልዕኮ አለመሆኑን ነገር ግን ምርምር በዚህ ጉዳይ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው ገልፀዋል፡፡

47. በሰብል እና በእንስሳት ዘርፎች የተገኙ የግብርና ውጤቶችን ግብይት ትስስር ለመፍጠር፣ አከባቢውን በይበልጥ ለማልማትና የህዝቡንም ባህል ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ተከናውኖ ተግባራዊ አለመደረጉ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ በገበያ ላይ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በማምረት ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ በማድረግ ካመረቱት የግብርና ምርቶች የተሻለ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን በልዩ ልዩ ብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋ ማስተዋወቅን በተመለከተ፡-

48. የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስን ለማስፋፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶች ወደ አምራቹ መድረስ፣ መሰራጨትና አመቺ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በልዩ ልዩ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የማስተዋወቅ ተግባር መከናወን ይኖርበታል፡፡

49. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት በግብርና ምርምር የተዘጋጁ የተለያዩ ማንዋሎች እንዲሁም ፓኬጆች በአከባቢው ቋንቋ ተተርጉመው ለባለድርሻ አካላት እና ለአርሶ አደሮች እንዲሰራጭ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በማዕከላቱ አከባቢ ለሚገኙ የግብርና ጽ/ቤቶች፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሞዴል አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

50. የተለያዩ ፓኬጆች እና የአሰራር ማንዋሎች በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ ብቻ የተዘጋጁ መሆኑ፤ በሌላ ቋንቋ (በሶማሊኛ፣ በአፋርኛ፣ በኦሮሚኛ…) እንዲዘጋጁ እና ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ አለመደረጋቸው ታውቋል፡፡ ለአብነት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-በቁሉምሳ፣ መልካሳ እና ወረር በእንግሊዘኛ ብቻ ከ11 በላይ የምርምር ውጤቶች ተዘጋጁ ቢሆንም አርሶ አደሮች ባግባቡ እንዲጠቀሙባቸው ለማስቻል በተጠቃሚዎቹ ቋንቋ ተዘጋጅተው እንዳልቀረቡ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከላይ በተጠቀሱት ማዕከላት በአማርኛ የተዘጋጁ የለውዝ፣ ሩዝ፣ የሰብል፣ የዳቦ ስንዴ፣ የባቄላ… አመራረት ዘዴ ማንዋሎች የተዘጋጁ ቢሆንም በተጠቀሱት አካባቢዎች በሚኖሩ አርሶ አደሮች የመግባቢያ ቋንቋ ተተርጉመው እንዳልቀረቡ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

51. የስምንቱም ማዕከላት የስራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከምርምር የተገኙ ውጤቶች አርሶ አደሮች በሚረዱት ቋንቋ ተተርጉሞ የማቅረብ ስራ እስከ አሁን ያልተገበሩት መሆኑን ነገር ግን በተለያዩ ሥልጠናዎች ላይ በትርጉም የሚያሰለጥኑ መሆኑና ይህን ተግባር ለማከናወን የበጀት እጥረት እንዳለባቸው ሆኖም ለወደፊት የሚያከናውኑት ተግባር መሆኑን እና በሆለታ የግብርና ምርምር ማዕከል የምርምር የሥራ ቋንቋው ከጅምሩ ጀምሮ በእንግሊዘኛ ይሰራበት ስለነበረ እንደሆነ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ በራሪ ወረቀቶች እንዲዘጋጁ መደረጉን ነገር ግን በማንዋል ደረጃ የተሰራ ሰፊ ሥራ አለመኖሩን ገልጸዋል ፡፡

52. የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በቴክኖሎጂ ትውውቅ ወቅት በራሪ ወረቀቶችን እና ሌሎች ህትመቶችን የሚጠቀሙ መሆኑን በአጠቃላይ በበቂ ሁኔታ ያልተሰራና ለወደፊት ለማከናወን ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

53. ከምርምር የተገኙ ውጤቶች አመቺ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በልዩ ልዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ቋንቋ የማስተዋወቅ ተግባር አለመከናወኑ የምርምር ውጤቶቹ ወደ አርሶ አደሮች በተገቢው መንገድ እንዳይተላለፉ በማድረግ አርሶ አደሮች ከምርምር ውጤቶች ሊያገኙት ይችሉ የነበረውን የተሻለ ግንዛቤና ውጤት እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

## የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአከባቢው የሚፈጥሩትን ተፅእኖ ለመቀነስ የሚጠኑ ጥናቶችን በተመለከተ፤

54. የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት…) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና መመሪያ እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል ጥናትና ምርምር ተከናውኖ ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ህብረተሰቡ ለጉዳት እንዳይዳረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡

55. የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና ሥርዓት እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል ምርምር መካሄድ እንዳለበት ሃገራዊ የግብርና ምርምር ፖሊሲና እስትራቴጂ የሚገልጽ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የምርምር ማዕከላት (ሆለታ፣አምቦ፣ ባኮ፣ አሶሳ፣ ደብረዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳና ወረር) ማዕከላት የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት…) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል ጥናት እንዳልተከናወነ ለማወቅ ተችላል፡፡ በተጠቀሱት ማዕከላት ከፀረ ተባይ ኬሚካሎች አጠቃቀም ጋር የተያያዘ የግንዛቤ ችግሮችን ለመቅረፍ የተሰሩ ስራዎች ባለመኖራቸው የአከባቢው ህብረተሰብ ኬሚካል የመጣባቸውን እቃዎችና በርሜሎች ለተለያዩ አገልግሎቶች (ለጋዝ፣ ለዘይት፣ ለውሃ…) የሚጠቀሙበት መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በማዕከላቱ አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች እና ሞዴል አርሶ አደሮች ጋር ከተካሄዱ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. የኢንስቲትዩቱ እና ስምንቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአከባቢ ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና መመሪያ ለማውጣት የሚያስችል ጥናትና ምርምር ያልተከናወነ መሆኑ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ያልተዘጋጁ መሆኑንና የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የቶክሲቶሎጂ ጥናትና ምርምር ስራ የሚያስፈልገው መሆኑንና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራም በስፋት መሰራት ያለበት በመሆኑ በግብርና ሚ/ር በኩል በአማካሪ ድርጅቶች ጥናት እየተጠና መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት…) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል በግብርና ምርምር ማዕከላቱ ጥናት ባለመደረጉ እና ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተዘጋጅተው የማንቃት ተግባር ባለመከናወኑ ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብና መመሪያ እንዳይወጣ ከማድረጉም በላይ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ኬሚካል የመጣባቸው እቃዎች ለቤት ውስጥ አገልግሎት እንዲውሉ በማድረግ የሰውን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡

## በኢንስቲትዩቱ ከግብርና ምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎችን በዕቅድ ማካሄዱን በተመለከተ፣-

58. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ምርምሮችን ለተጠቃሚው ለማድረስ የሚከናወኑ ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እና ውጤታቸውም መለካት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለምርምር ውጤት ተጠቃሚው የተሰጡ ሥልጠናዎች በሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ውስጥ አፈጻጸማቸው ከዕቅድ ጋር ተነጻጸሮ የማይቀርብ መሆኑ፣ ሥልጠናዎች የሚለኩበት ወጥ የሆነ የመከታተያ ሥርዓት አለመኖሩ እና ግብረመልስ የማይሰጡ መሆኑ እንዲሁም ሥልጠናዎች በወቅቱ የማይሰጡ በመሆናቸውን አንዳንዴ የአዝመራ ወቅት ካለፈ በኋላ የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩና በአንድ /በተመሳሳይ/ ሥልጠና ላይ አንድ ሰው በተደጋጋሚነት በስልጠናው እንደሚሳተፍ ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. በቁሉምሳ ምርምር ማዕከል በ2006 ዓ.ም በእንስሳት ምርምር የሥራ ሂደት የታቀደ ሥልጠናው ለሌላ ጊዜ የተላለፈ መሆኑን፣ በአሶሳ በኩይሳ አርሶ አደሮች ለስልጠና ተመዝግበው በወቅቱ ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ እና በወረር በበግ፣ በፍየል፣ በስንዴ፣ በሰሊጥ፣ በመኖ ዘሮች እንዲሁም በማዳቀል ሥራ ዙሪያ ሥልጠና የተሰጣቸው ቢሆንም ግብረመልስ ያልተሰጠ መሆኑን በአፋር ክልል አሚባራ ወረዳ በበዱላአሌ ቀበሌ ገበሬ ማህበር አከባቢ ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

61. የፌዴራል ግብርና ምርመር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ ስልጠና በወቅቱ ያልተሰጠበት ምክንያት በጀት በወቅቱ የማይለቀቅ በመሆኑና ሰልጣኞቹም ስልጠና ከወሰዱ በኋላ ወደ ተግባር እንዲገቡ ያልተደረገበት ምክንያት ደግሞ አርሶ አደሩ፣አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮቹ ማሟላት የሚገባቸውን እንደ መሬትና የመሳሰሉት ባለሟሟላታቸው ሲሆን እንዲሁም በየዓመቱ የሚሰጡ ስልጠናዎች የምርምር ዕቅድ ጋር የሚታቀዱ ሲሆን ሥልጠናን ከንውን ሪፖርት ዕቅዱ ጋር በንጽጽር የማይቀርብ በመሆኑ ሥልጠናዎቹ ያመጡት ለውጥ ለመለካት ያለመቻሉ ነገር ግን ይህ ክፍተት ለወደፊቱ መስተካከል የሚገባው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

62. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ከምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸው ለአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ስልጠናው የግብርናውን ምርታማነት ለማሳደግና ሊኖር ይችል የነበረውን አስተዋፅኦ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ስልጠናዎች ያስገኙትን ውጤት አለመለካቱ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የወሰዳቸው ስልጠናዎች ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን በመመዘን መሻሻል የሚገባቸውን ጉዳዮች በወቅቱ በመለየት የሚሰጡ ስልጠናዎች ፋይዳ እንዳይጎለብት ያደርጋል፡፡

## በኢንስቲትዩቱ የልቀት(Center Of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Centers) ማዕከላት በጥናት የተመረጡ መሆኑን በተመለከተ፡-

63. በኢንስቲትዩቱ የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Center) ማዕከላት ሲመረጡ ግልጽ የሆነ መስፈርት (Criteria) ሊያወጡ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ እንዲሁም ለአርሶ አደሩ፣ለአርብቶ አደሩ እና በከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ የልቀት ማዕከል ሊኖር ይገባል፡፡

64. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ ማዕከላት የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Center) ተብለው የተለዩ ማዕከላት የተመረጡበትን መስፈርት በግልፅ የሚያሳይ ማስረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡ እንዲሁም የልቀት ማዕከላቱ ስህነ ምህዳርን፣ የህብረተሰቡን አመራረት ሁኔታ፣ የማዕከላቱን ማስፈጸም አቅም ወ.ዘ.ተ መሰረት አድርገው ያልተመረጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለምሳሌ፡- በመልካሳ የምርምር ማዕከል የስራ ስር፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የቆላ ጥራጥሬ፣ ማሽላ፣ ሜካናይዜሽን እና የሃር ትል ልቀት ማዕከል ሲሆን፣ የደብረዘይት የምርምር ማዕከል ደግሞ የዶሮ፣ የሆለታ የወተት ከብት እርባታ (Dairy) ፣ የአምቦ የምርምር ምዕከል እጽዋት ጥበቃ… የልቀት ማዕከል ሆነው የተመረጡ መሆኑ ተገልፃል፡፡ በሌላ መልኩ የማንጎ ምርት በስፋት በአሶሳ አካባቢ የሚገኝ ቢሆንም ማስተባበሪያው የሚገኘው የማንጎ ምርት በስፋት በማይመረትበት በመልካሳ ምርምር ማዕከል መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ የእንስሳት ሃብት የልቀት ማዕከላት እንዳልተቋቋሙ ታውቋል፡፡

65. ስምንቱም በናሙና የታዩ የግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የልቀት ማዕከላት ሲመረጡ የራሳቸው የሆነ ምክንያት ያላቸው ቢሆንም ነገር ግን የመምረጫ መስፈርቶችን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ማቅረብ የማይችሉና የመረጃ አያያዝ ሥርዓታቸው ክፍተት ያለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአጠቃላይ በምርምር ሥርዓት አደረጃጀት ችግር ምክንያት የልቀት ማዕከል ጽንስ ሀሳብና አሰራር በምርምር ማዕከላቱ ተግባራዊ ያልሆነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

66. በኢንስቲትዩቱ የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Center) ማዕከላት ሲመረጡ ግልጽ የሆነ መስፈርት (Criteria) ባለመኖሩ የተለያዩ ማዕከላትም ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ወደ ምርምር ተግባር አለመግባታቸው በምርምር ማዕከላቱ የሚገኙ ተመራማሪዎች የሥራ ተነሳሽነትን ለማሳደግ እና የተለያዩ ማዕከላት የምርምር ውጤቶቻቸውን በሀገር ውስጥ፣ በክፍለ አህጉሩና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን በትጋትና በጥራት ለመስራት እንዳይበረታቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## በግብርና መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮች በአጭር ጊዜ ወደ ተግባር ሊሸጋገሩ የሚችሉ መሆኑን በተመለከተ፡-

67. የፌዴራል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በግብርና መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮች በአጭር ጊዜ ወደትግበራ ሊሸጋገሩ የሚችሉ፣ የሚፈለገውን ውጤት የሚሰጡና በአነስተኛ ወጪ ምርትን የሚያሳድጉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይኖርበታል፡፡

68. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት ተግባራዊ እና ተግባራዊ ያልሆኑ እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውጤት ሊሰጡ የሚችሉና የማይችሉ ተብለው ተለይተው በዕቅድ እንዲያዙ የማይደረጉ እና አፈጻጸማቸውም በዚሁ መልክ እንደማይቀርብ ለማወቅ ተችሏል፡፡በተለይ በእንስሳት ዘርፍ የሚያዙ ዕቅዶች አብዘኛዎቹ በረጅም ጊዜ ላይ የሚያተኩሩ እና በእንስሳት ዘርፍ በነባር ዝርያዎች ላይ የሚደረጉ ምርምር ሥራዎች በአብዛኛው ውስን መሆናቸው ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በምርምር የተለዩ ቴክኖሎጂዎች ከቀረበ/ከተሰራጨ በኋላ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ወደተግባር ሲገቡ በምን መልኩ ቢከናወኑ ወጪያቸውን ለመቀነስ እንደሚቻል የሚያመላክቱ ጥናቶች በማዕከላቱ እንደማይከናወኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ በሽታን የሚቋቋሙ የስንዴ ዝርያዎች በብዛት አለመኖራቸው እንዲሁም የመሬትን ለምነት ሊጠብቁ እና የፀረ- አረም ወጪን መቀነስ የሚችሉ (ኮምፖስት፣ ቬርሚ ኮምፖስት፣ አረምን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን በማፍለቅ…) ቴክኖሎጂዎችን በስፋት

በማሰራጨት አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዳልተደረገ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የምርምርና የፊዚካል ውጤቶች ማቅረቢያ ሪፖርት፣ ለአከባቢው ሞዴል አርሶ አደሮች፣ ግብርና ጽ/ቤቶች፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና ለምርምር ማዕከላት ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. በናሙና ተመርጠው ለታዩት የግብርና ምርምር ማዕከላት የሥራ ኃላፊዎች በየኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የምርምር ሥርዓቱ ያመጣቸው አዲስ የሰብል ዝርያዎች በአጭር ጊዜ ውጤት ሊሰጡ የሚችሉ አሉ፡፡ ነገር ግን ለወደፊት በስፋት መሰራት ያለበት መሆኑን እና በምርጥ ዘር ወጪ ላይ ሚና ያላቸው ሌሎች/የብዜት አካላት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአጠቃላይ በዋናነት በማዕከላቱ የሚሰራው ተግባራዊ ምርምር መሆኑን ገልፀው፤ ሆኖም ግን የእንስሳት ምርምር በባህሪው ጊዜ ወሳጅ ቢሆንም ጊዜውን ለማሳጠር በባዮቴክኖሎጂ ምርምር ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አረምን የሚቋቋም ዝርያ ማውጣት በተመለከተ ደግሞ በሁሉም ሰብሎች ተግባራዊ ማድረግ የሚቻል ባይሆንም በአቀንጭራ አረም ዙሪያ ውጤታማ የሆኑ የማሽላ ዝርያዎች መውጣታቸውን እና በሽታን መቋቋም የሚችሉ የስንዴ ዝርያዎች ያሉ ቢሆንም በሽታው ስለሚቀያየር አዳዲስ ዝርያዎችን በየጊዜው ማውጣት እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል፡፡

70. የግብርና ምርምር ማዕከላቱ በግብርና መስኮች የሚያካሂዱቸው ምርምሮች ተግባራዊ እና በአጭር ጊዜ ውጤት የሚሰጡ ምርምሮች ላይ ትኩረት አድርገው አለመስራቻቸው የምርም ውጤቶች ጊዜ ረጅም እንዲሆንና ወጪያቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በአነስተኛ ወጪ ምርትን የሚያሳድጉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ አለመሰራቱ ከሞዴል አርሶ አደሮች ውጪ የሆኑ እና አቅመ ደካማ የሆኑ አርሶ አደሮች፣አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ከምርምር ማዕከላት በሚወጡ ቴክኖሎጂ ላይ በስፋት ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

## በግብርና ምርምር የሚቀርቡ ቴክኖሎጂዎች መነሻ ሃሳብ አመራረጥን በተመለከተ፡-

71. በግብርና ምርምር ማዕከላቱ የሚካሄደው የግብርና ምርምሮች የሚቀርቡ ቴክኖሎጂዎች ከአርሶ አደሮች ተጨባጭ ችግሮች የሚነሱ እና ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት መስፈርት ወጥቶላቸው የችግሮቹን አንገብጋቢነትና ተቋሚዊ የማስፈፀም አቅምን ያገናዘቡ እና የባለድርሻ አካላትን ስምምነት ያገኙ ሆነው የተመረጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

72. ለግብርና ምርምር የሚቀርቡ ቴክኖሎጂዎች ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግሮች የማይነሱ እና የባለድርሻ አካላትን ስምምነት እንዲያገኙ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የግብርና ምርምር አማካሪ ካውንስል ADPLAC ቃለ-ጉባኤዎች፣ በናሙና ለተመረጡ አርሶ አደሮች፣አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች፣ የዞን እና የወረዳ የግብርና ጽ/ቤት ባለሙያዎች፣ ለግብርና ጽ/ቤቶች፣ በምርምር ኤክስቴንሽን የአርሶ አደሩ ግንኙነት፣ ለግብርና ኢኮኖሚክስ ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተካሄደ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

73. በአርሶ አደሮች አካባቢ በስፋት የሚታዩ የእንስሳት ጤናና የመኖ አቅርቦት ችግሮች እና የሰብልና የእፅዋት በሽታዎች በስፋት የሚታዩና በምርምር መፍትሂ እንዲፈለግላቸው ጥያቄ ከቀረበባቸው ጉዳዮች መካከል ለአብነት ያህል በቁሉምሳ ምርምር ማዕከል በእንስሳት እርባታ/ዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ፣ በተፈጥሮ ግጦሽ ማሻሻያ ዘዴ፣ በእንስሳት መኖ ችግሮች ላይ፣ በእንስሳት ተዋጽኦ፣ በእንስሳት ጤና፣ በበቆሎ ዘር ዙሪያ፤ በሆለታ የግብርና ምርምር ማዕከል በቁጥር 26/18/3074/2005 በመስከረም 22/2005 ዓ.ም የምርምር ፍላጎታቸውን እንዲገልፁ በተጻፈላቸው ደብዳቤ መሰረት ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የጥቁር አፈር ምርታማነት መቀነስን፤ የጉራጌ ዞን የአፈር ኮምጣጣነትን (Soil Acidity) ፣ በስምንት ወረዳዎች ላይ ውርጭ የተከሰተ መሆኑን እና በስልጤ ዞን የአፈር ለምነት እና የማዳበሪያ አጠቃቀም ችግሮች ተገልፀዋል፡፡በተመሳሳይ መልኩ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ስብሰባ ላይ ከተነሱት ጥያቄዎች መካከል

ለአብነት ያህል፡- የስንዴ ዝርያዎች በዋግ በሽታ መመታት፣ ሙሎ ወረዳ አከባቢ በንብ ማነብ የተሰማሩ አርሶ አደሮች ንቦችን የሚያጠፉ ወፎች መኖራቸው ተጠቁሟል፡፡ በአምቦ የግብርና ምርምር ማዕከል የእንስሳት በሽታ፣ የበርበሬ ቫይራል በሽታ እና የማንጎ በሽታ (White scale mango)፤ በወረር የግብርና ምርምር ማዕከል በእንስሳት እርባታ/ዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ፣ በተፈጥሮ ግጦሽ ማሻሻያ ዘዴ፣ በእንስሳት መኖ ችግሮች ላይ፣ በእንስሳት ተዋጽኦ፣ በእንስሳት ጤና ላይ እና በበቆሎ ዘር ዙሪያ የተገለጹ ችግሮች ቢሆኑም እነዚህን የአርሶ አደሩን ችግሮች ከመፍታት አንጻር የግብርና ማዕከላቱ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉና በነዚህ ችግሮች መነሻነት የተካሄዱ የምርምር ስራዎች አነስተኛ መሆኑን በምርምር ማዕከላቱ አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች እና የዞን እና የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ባለሙያዎች ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከተሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

74. እንዲሁም በመልካሳ አከባቢ አርሶ አደሮች የእርሻ መሳሪያ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ በተደጋጋሚ ቢገልፁም በእርሻ መሣሪያዎች ብዜትና ሥርጭት የሥራ ሂደት የቢቢኤም ብዜት፣ የጤፍ መውቂያ፣ የመኖ መከርተፊያና የፓፓያ ማውረጃ፣ የበቆሎ መፈልፈያ፣ የጤፍ መውቂያ መሳሪያ በማምረት ችግሮቹ እንዲፈቱ ያልተደረገ መሆኑ ከእርሻ መሣሪያዎች ብዜትና ሥርጭት ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

75. በደብረዘይት ከዶሮ እርባታ እንዲሁም በመልካሳ ከሃር ትል እርባታ ጋር በተያያዘ ከተሰራው ሥራ ውጭ በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የግብርና ምርምር ማዕከላት ተጠንተው የሚቀርቡት ቴክኖሎጂዎች ባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ማለትም የሥርዓት- ፆታን፣ አረጋዊያንን፣ ወጣቶችንና ኤች አይ ቪንና የመሳሰሉትን ላይ በማተኮርና በማካተት የማይጠኑ እና ለነዚህ አካላት የሚውል ቴክኖሎጂ ውጤት እንዲኖር አለመደረጉ ታውቋል፡፡ እንዲሁም የምርምር የመፍትሄ ሀሳቦች የተሻሉትን ለመምረጥ የሚያስችል ተገቢውን መስፈርት ማለትም የችግሩን አንገብጋቢነት፣ ተቋሚዊ የማስፈፀም አቅም ያገናዘበ መፍትሄ በማውጣት ትኩረት የሚደረግባቸው የምርምር ጉዳዮች ተለይተው እንደማይያዙ በኦዲቱ ከታዩት የስምንቱ ማዕከላት ለመረዳት ተችሏል

76. ስለጉዳዩ የፌዴራል ግብርና ምርመር ማዕከላት የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ልዩ ትኩረት የሚሹ ተብለው የሚቀርቡ ቴክኖሎጂዎች ላይ ብዙ የተሰሩ ሥራዎች አለመኖራቸውን ገልፀዋል፡፡ ለሥርዓተ ፆታ፣ አረጋውያንን፣ ወጣቶችንና ኤች. አይ ቪ ን ያካተቱ ምርምሮች ለመስራት  የሚያስችል ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ አስረድተዋል፡፡ ነገር ግን በሥልጠና ወቅት የሴቶች ተሳትፎ እንዲኖር የሚደረግ መሆኑን እንዲሁም ከአርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ተጨባጭ ችግሮችን ለመለየት ያልተቻለበት ዋና ምክንያት የባለድርሻ አካላትና የግብርና ምርምሩ የሚገናኙበት መደረክ  የላላ በመሆኑና ሁሉም አካላት የማይሳተፉበት ሁኔታ በመኖሩ እና በወረር እና በአሶሳ ማዕከላት ደግሞ ግንኙነቱ ሙሉ በሙሉ በመቋረጡ  የተፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

77. በግብርና ምርምር የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግር የሚነሱ ባለመሆናቸው የተጠቃሚዎቹን ፍላጎት የማያረኩና ችግሮቻቸውን የማይቀርፍ የተጠቃሚዎቹን ተሳትፎ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በምርምር ስራ እንዲካተቱ የሚያስችሉ መስፈርቶች ወጥቶላቸው አለመከናወናቸው የምርምር ውጤቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎችን ትኩረት በመስጠት እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የሚውል ቴክኖሎጂ የቀረበ መሆኑን በተመለከተ፡-

78. በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች አገልግሎት የሚውል (ከአቅም፣ ፍላጎታቸው እና እድገታቸው) ጋር ሊጣጣም የሚችል ቴክኖሎጂ ሊቀርብ ይገባል፡፡

79. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የቀረቡ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ እና በግብርና ሥራ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ተብሎ ተለይቶ የተሰራጨ ቴክኖሎጂ አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ከማዕከላቱ ማኔጅመንት አባላት ጋር በተደረገው ስብሰባ ከተያዘ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

80. የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በምርምር ሥርዓት ውስጥ ከአርሶ አደሮች፣አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ውጪ ለባለሃብቶች የሚመጥን ቴክኖሎጂ የሚሰራበት አሰራር የሌለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

81. በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች አገልግሎት የሚውል/ አቅምና ፍላጎታቸው ጋር ሊጣጣም የሚችል ቴክኖሎጂ ሊቀረፅና እድገታቸውን በማገናዘብ የሚመጥን ቴክኖሎጂ እንዲጎለብት ባለመደረጉ አገሪቱ በግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቶጂዎችና ሥልቶች ላይ ለውጥ የሚያመጡ ቴክኖሎጂዎች እንዳይፈጠሩ እና የግብርናውን ዘርፍ ወደ ኢንዱስትሪ የመለወጥ ሂደቱን እንዲዳከም ያደረገዋል፡፡

## ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ቴክኖሎጂ በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት ፍተሻ መደረጉን በተመለከተ፡-

82. የግብርና ምርምር ማዕከላት የተሻሻሉ የግብርና ግብዓቶች የአገሪቱን ህግና ደንብ ተከትሎ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ማንኛውም ቴክኖሎጂ በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት ፍተሻ ከተካሄደ በኋላ በምርምር ማዕከል ደረጃ የማላመድና የምርታማነት ብቃት ፍተሻ ሊከናወን ይገባል፡፡

83. በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ተመርጠው በታዩት በስምንቱም ማዕከላት ከውጭ አገር የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች በኳራንቲን ቆይታው ከበሽታ ነፃ መሆናቸው የማረጋገጥ ስራ በተጠናከረ ሁኔታ እንደማይካሄድ ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. በመልካሳ የግብርና ምርምር ማዕከል የጠበቀ ፍተሻ ባለመኖሩ በአገራችን ያልተለመዱ ተባዮችና በሽታዎች ወደ ሃገራችን ገብተው ጉዳት ያስከተሉበት ሁኔታ ተከስቷል፡፡ (ለማሳያ፡- የቲማቲም ቅጠል ሰርሳሪና ፍሬ ቦርቧሪ ተባይ ሊጠቀስ መቻሉ፤) እንዲሁም በወረር ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከውጭ የሚመጡ ዝርያዎችና ቴክኖሎጂዎች ወደ ማዕከሉ ስለሚገቡበት ሁኔታ በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት በባለድርሻ አካላት እና በተመራማሪዎች ወደ

ማዕከሉ የገቡ የጥጥ ዝርያዎች እና ቴክኖሎጂዎች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው ባለመግባታቸው በተፈጥሮ እና በተጠቃሚዎች ላይ ጉዳትና ኪሳራ ያስከተሉ መሆኑን በ25/07/05 ዓ.ም ከተፃፈ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ክትትል የተደረገላቸው እና ከበሽታ ነፃ መሆናቸውን የሚያመለክት ሪፖርት በማስረጃነት ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

85. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ እና የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት የስራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የኳራንቲንን ስራ ለማከናወን የጠበቀ ኃላፊነት ያለበት የግብርና ሚ/ር መሆኑን፣ በወረር የተከሰተው ከጥጥ ጋር በተያያዘ ችግር በአንድ የህንድ ካምፓኒ አማካኝነት መሆኑን እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ ግለሰቦች የግብርና ምርቶች ደብቀው የሚያስገቡዋቸው ስላሉ መንግሥት በዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት የገለፁ ቢሆንም ማዕከላቱ የተለያዩ በሽታዎች ከመከሰታቸው እና አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ጋር ከመሰራጨታቸው በፊት የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እንደማይሰራ የተሰበሰቡት መረጃዎች ስለሚያረጋግጡ ኢንስቲትዩቱና የምርምር ማዕከላቱ የበላይ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ የሰጡት መልስ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

86. ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት የተለያዩ በሽታዎች እንዳይከሰቱ እና እንዳይሰራጩ የሚደረግ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት የላላ በመሆኑ በአገራችን የሌሉ አዳዲስ በሽታዎች እንዲሰራጩ፣ የግብርና ምርቶች እንዲጠፉና እንዲበላሹ በማድረግ የአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩን የግብርና ውጤቶች እንዲቀንሱ በማድረግ የግብርና ምርምርና በምግብ ራስን የመቻል ስትራቴጂ የታሰበውን ያህል ውጤት እንዳያመጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፕሮጀክቶች፣ ግንባታዎች እና የምርምር ተግባራት በታቀደላቸው በጀት እና ጊዜ የተጠናቀቁ መሆኑን በተመለከተ፡-

87. በፌዴራል የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች፣ ግንባታዎች እና የምርምር ተግባራት የሚጀመርበት እና የሚጠናቀቅበት ጊዜና ወጭ

በአግባቡ ሊታቀድ፣ በተያዘለት ዕቅድ መሰረት በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም አስፈላጊው ድጋፍ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

88. በኦዲቱ ወቅት በታዩት ስምንቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት እንዲከናወኑ የተደረጉ የምርምር ተግባራት በጥልቀት የሚፈጁት የገንዘብና የሀብት መጠን ተተምኖ በቅድሚያ የማይለይና በፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም ሂደት ላይም ከአፈጻጸማቸው ጋር እንዲነፃፀሩ የማይደረግ ሲሆን እያንዳንዳቸው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት አጠቃላይ የፈጁት ወጪ እና ጊዜ ከዕቅዱ ጋር በማነፃፀር የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን የፕሮጀክቶቹን ግምገማ በወቅቱ ስለመከናወኑ የሚያሳዩ መረጃዎች በኦዲቱ በታዩት የምርምር ማዕከላት ለኦዲት ቡድኑ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

89. በሌላ መልኩ በወረር እና በአሶሳ የግብርና ምርምር ማዕከላት ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸውና ከሶስት አመት በፊት ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የነበረባቸው በማዕከሉ የሚገኙ ህንጻዎች አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲሁም አገልግሎት መስጠት ሳይጀምሩ ለመፍረስ፣ ለመሰነጣጠቅ… እየተዳረጉ መሆኑን እና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ክትትል ተደርጎ ውሳኔ እንዳልተሰጠበት ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወረር የግብርና ምርምር ማዕከል የሚገኝ የፓንፕ ሳይት ግንባታ በጥናት ላይ ተመስርቶ የተገነባ ባለመሆኑ ከ2003-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 2,000,000 ብር (ሁለት ሚሊዮን ብር) ወጪ ተደርጎበት በ2006 ዓ.ም ግንባታው እንዲቆም የተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

90. እንዲሁም ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩት የምርምር ማዕከላት ውስጥ በአራቱ ማዕከላት (በሆለታ፣ መልካሳ፣ ወረርና ቁሉምሳ) ብቻ 63 የምርምር ተግባራት እንዲቋረጡ መደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ ከሚመለከታቸው የማዕከላቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ እና በመስክ ጉብኝት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የተቋረጡ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

| የሙከራው ዓይነት | በ2004 ዓ.ም የተቋረጡ ብዛት | በ2005 ዓ.ም የተቋረጡ ብዛት | በ2006 ዓ.ም የተቋረጡ ብዛት |
|---|---|---|---|
| አተክልትና ፍራፍሬ | 1 | - | - |
| ባዮ ቴክኖሎጂ | - | 4 | 2 |
| እንስሳት ምርምር | - | 2 | 6 |
| ባዮሜትሪክስ ጂአይ ኤስና አግሮ ሜትሮሎጂ | 1 | - | - |
| ብዕርና አገዳ ሰብሎች | - | 21 | 3 |
| ስራ ሥር አተክልትና ፍራፍሬ | - | - | 9 |
| ጥራጥሬ፣ ቅባትና ጭረት ሰብሎች | 8 | - | - |
| በፓቶሎጂ(ጥጥና ለውዝ) | - | 4 | - |
| የአዲስ ማዳበሪያ ጥናቶች | - | 2 | - |
| ድምር | 10 | 33 | 20 |

91.በሌላ መልኩ በአምቦ የግብርና ምርምር ማዕከል ምርምር የሚካሄድባቸው በበቆሎና የሸንኮራ አገዳን የሚያጠቁ ቫይረሶች ላይ የሚካሄዱ ምርምሮችና በቲማቲም፣በቃሪያና በሽንኩርት ላይ የሚካሄዱ ምርምሮች እየተካሄዱ የነበሩ ሶስት የግብርና ተግባራት (Activities) እንዲዘገዩ መደረጉን ለማወቅ ተችላል፡፡

92.እንዲሁም በአሶሳ ግብርና ምርምር ማዕከል በሰብል እና እንስሳት ዘርፎች የሚቀርቡ የምርምር ውጤቶች አቅርቦት መዘግየት እንደሚታይባቸው ለመረዳት ተችላል፡፡ በተለይም ችግሩ በመንደር 14 እና 28 አከባቢ የሚኖሩ አርሶ አደሮች በምርምር ማዕከሉ መሬት አዘጋጁ እና በሙያ እያገዝናችሁ አብረን እንዘራለን ተብለው የመዝሪያው ወቅት እንዲያልፍባቸው የተደረጉ መሆኑን አርሶ አደሮቹ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡





ፎቶ ቁጥር አንድ በፌዴራል ግብርና ምርመር ኢንስቲትዩት በወረር ማዕከል አገልግሎት ሳይሰጡ ለሌላ ችግር እየተጋለጡ የሚገኙ የቤት እና የፓንፕ ሳይት ግንባታዎች፤

93. የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አብዛኛዎቹ የምርምር ተግባራት ሊቋረጡ የቻሉት በተመራማሪዎች መልቀቅ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ኬሚካል እና ሪኤጅንት በማጣት ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ተመራማሪዎቹ ለትምህርትና ሥልጠና በመሄዳቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ግንባታዎቹ አገልግሎት መስጠት ያለመጀመራቸው በተመለከተ ደግሞ ግንባታዎቹን ያስጀመረው ኢንስቲትዩቱ በመሆኑ ስለጉዳዩ ኢንስቲትዩቱ መልስ መስጠት ያለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

94. የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ቡድኑ ስለጉዳዩ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ የምርምር ተግባራት በግለሰብ ችግር እና በተለያዩ ምክንያቶች የሚቋረጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ግንባታዎች የሚቋረጡት በዋናነት በኮንትራክተሮች ችግር መሆኑንና የወረር የግብርና ምርምር ማዕከል የፖንፕ ሳይት ግንባታ ጉዳይ ከዲዛይን ጋር በተያያዘ ከአዋሽ ሸለቆ ተፋሰስ ጋር በተፋሰስ ጉዳዮች እንዲቋረጥ አስተያየት ስለተሰጠበት ውሳኔ ባለማግኘቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ግንባታዎች፣ ፕሮጀክቶች እና የምርምር ተግባራት በጥናት ላይ ተመስርተው እንዲታቀዱ እና በዚሁ መስረት ተግባራዊ ባለመደረጋቸው የተከሰቱ ችግሮች በመሆናቸው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ የሰጡት መልስ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

95. ፕሮጀክቶች፣ ግንባታዎች እና የምርምር ተግባራት በታቀደላቸው በጀት እና ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማስቻል በተገቢው ጥናት ላይ ተመስርተው እንዲታቀዱ በማድረግ በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ወቅታ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ በስራ ሂደቱ ለሚያጋጥሙ ችግሮች አፋጣኝ መልስ ባለመስጠቱ የምርምር ስራዎች በአግባቡ ተከናውነው ከምርምሮቹ እንዲገኝ የሚጠበቀው ውጤት እንዳይገኝ በማድረግ ፕሮጀክቶችና ግንባታዎቹ መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት በሚፈለጉበት ጊዜ እንዳይሰጡ እና ለግንባታዎቹ የሚያስፈልገው ጥገና፣ ክትትልና እንክብካቤ በወቅቱ እንዳይደረግላቸው በማድረግ ግንባታዎቹ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎቶች እንዳይሰጡና ለስራው የተመደበው ሀብትና ጊዜ ያለአግባብ እንዲባክን አድርጓል፡፡

## በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ ወይም የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች ማስረጃዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆናቸውን በተመለከተ፡-

96. ኢንስቲትዩቱ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ ወይም የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች፣ በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት እና በምርምር ሥራ ላይ የተሰማሩ ወይም የሚሰማሩ አካላት በሰራ ላይ እንዲያውሏቸው እነዚህ ተቋማትን መዝግቦ በመያዝ የምርምር ውጤቶቹን ለሚፈልጉ አካላት ሊሰጥ ይገባል፡፡

97. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱን የግብርና ምርምር ማዕከላት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ ወይም የሚካሄዱ ምርምሮች ፣ በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት እና በምርምር ሥራ ላይ የተሰማሩ ወይም የሚሰማሩ የተለያዩ ተቋማት በኢንስቲትዩቱ በማዕከላዊነት ተመዝግበው እንዳይያዙ በማድረግ የምርምር ውጤቶች በእነዚህ ተቋማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ እንዳልተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከ2004 -2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ 17ቱም ማዕከላት ያወጡትን የምርምር ውጤቶች ማስረጃ በማዕከላዊነት በኢንስቲትዩቱ እና በየማዕከላቱ ተጠናቅሮ ያልተቀመጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተካሄዱ የዶክሜንት ክለሳዎች እና ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

98. ስለጉዳዩ የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ቡድኑ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩቱ ማስረጃዎችን የማጠናቀር ኃላፊነት ቢኖርበትም ያልተተገበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በአጠቃላይ በምርምር ሥርዓቱ የመረጃ አያያዝ ክፍተት ያለበት መሆኑን አስረድተዋል፡፡የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ይህ ጉዳይ በአዋጁ ላይ የሰፈረ ቢሆንም አገራዊ የምርምር ሥርዓት ለመምራት (EIAR) አመቺ ስላልነበረ በአብዛኛው አለመፈጸሙን ገልጸዋል፡፡

99. በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ/ የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች በማስረጃነት ተይዘው ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ የምርምር ውጤቶች እንዳይስፋፉ ከማድረጉም በላይ ተጠቃሚው የሚፈልገውን የምርምር ውጤት መርጦ እንዳይጠቀም እና የምርምር ውጤቶችን ለማሻሻል ሪፈረንስ እንዳይኖር ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት ተመዝግበው አለመያዛቸው የምርምር ውጤቶች በትክክል ለየትኞቹ ብዜት ተቋማት መሰራጨት እንዳለበት እንዳይታወቅ በማድረግ የምርምር ውጤት ተደራሽነት ላይ ተጽኖ ያሳድራል እንዲሁም በምርምር ሥራ ላይ የተሰማራ/ የሚሰማራ ማንኛውም አካል ተመዝግቦ አለመያዙ እና የሚተገብረው ሥራ አለመታወቁ የምርምር ሥራ በተደጋጋሚነት እንዲከናወን ከማድረጉም በላይ የተለያዩ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ አዳዲስ ዝርያዎች ምክንያት በሽታዎች እና ተባዮች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በር ይከፍታል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በግብርና ምርምር ማዕከላት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡-

100. ኢንስቲትዩቱ የግብርና ምርምር ማዕከላትን የዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀማቸውን የሚገመግምበት እና ግብረ መልስ የሚሰጥበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኢንስቲትዩት ስር የሚገኙ የምርምር ማዕከላትም በዕቅድ የሚይዛቸውን ስራዎች ውጤታማነት ለማረጋገጥ በአፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችና በወቅቱ ለይቶ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

101. ኢንስቲትዩቱ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ ስምንቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት የዕቅድ አፈጻጸም ሂደት በታቀደው መሰረት መሆኑንና የሚጠበቀውንም ውጤት ከያዙት ግብ አንጻር ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ ክትትልና ግምገማ መከናወኑን ለማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት ከሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

102. በሌላ መልኩ የግብርና ምርምር ማዕከላቱ በዕቅድ የያዟቸውን ተግባራት አፈፃፀም ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ በማድረግ በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮችን አፋጣኝ መፍትሄ ስለመስጠታቸው ለማረጋገጥ በኦዲት ወቅት በምርምር ማዕከላቱ ከተከለሱ መረጃዎች ለስራ ኃላፊዎችና በአካባቢው ለሚገኙ አርሶ አደሮች ከተደረጉ ቃለ መጠይቆችና የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡- በግብርና ምርምር ማዕከላቱ ለአርሶ አደሩ፣አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ለሙከራ የሚሰራጨው ዘር ከመዝራት እስከ አጭዶ ሰብስቦ ማስገባት ደረስ ያለው ሂደት የክትትልና ቁጥጥር ሥራ የተጠናከረ አለመሆኑ፣በማዕከላቱ ለአከባቢው ለግለሰብ የሚሸጠው ዘር ግለሰቡ ያለው መሬት ሳይጣራ የሚሸጥላቸው በመሆኑ ግለሰቦች መልሰው ለአርሶ አደሩ በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጡበት ሁኔታ መኖሩ፣በማዕከላቱ የተለያዩ የምርምር ተግባራት በሰው ሃይል አለመሟላት ምክንያት ሲቋረጡ ተከታትሎ ለማስቀጠል የሚደረገው ጥረት አነስተኛ መሆኑና በቡድን ሊሰሩ የሚችሉ የምርምር ስራዎችን ተመራማሪዎች በቡድን እንዲያከናውኑ እንደማይደረግ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በማዕከላቱ አከባቢ በምርምር ተግባር ላይ በማዕከላቱ አከባቢ ድንገት የሚከሰቱ ሁኔታዎችን (Emerging issues) /የመኖ እጥረት፣ የተባይና በሽታ ክስተቶች…/ በሚካሄዱ የምርምር ስራዎች ላይ የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስና የአርሶ አደር፣ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩን ችግር ለመፍታት በምርምር ተቋማቱ የሚደረጉ ጥረቶች የተጠናከሩ እንዳልሆነ በኦዲት ወቅት ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው በማዕከላቱ አከባቢ ከሚገኙ ሞዴል አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመረዳት ተችሏል፡፡

103. በወረር የግብርና ምርምር ማዕከል በ2006 ዓ.ም የጥጥ ላብራቶሪን የምርምር ማዕከሉ ተከታትሎ ሥራ እንዲሰራ ባለማድረጉ ስራው እንደተቋረጠ ታውቋል፡፡

በ2004 ዓ.ም በዚሁ የግብርና ምርምር ማዕከል ለአርሶ አደሮች ለማሰራጨት የታቀዱና የተባዙ የመኖ ዝርያዎች (ሮደስ፣ ፓኒከም፣ሲንክረስ/በፍል፣ ዝሆን ሳር፣ አልፋ አልፋ፣ ላብላብ፣ ለም አተር፣ ሰስባኒያና ሉኪኒያ) 20.2 ኩንታል ዘር እንዲሁም የዝሆን ሳር 50,000 (አምሳ ሺ) ቁርጥራጭ የተባዛ ቢሆንም ለአርሶ አደሮች እንዳልተሰራጨ ታውቋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በ2005 ዓ.ም የስንዴ (ደንደአ፣ ሽሪማ፣ ሀዳሴ-5595 ፣አጎልቾ-5520፣ ዲገሉ፣ ቀቀባ እና ጋአምቦ) 278.45 ኩንታል የተባዛ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ለአርሶ ፣ አርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደሩ እንዲሰራጭ እና ጥቅም ላይ እንዲውል አለመደረጉ ታውቋል፡፡

104. በመልካሳ የግብርና ምርምር ማዕከል በ2004 ዓ.ም ዕቅዱ ከአፈጻጸሙ ጋር ሲነጻጸር የባዮቴክኖሎጂ ሰብል ጥበቃ አፈጻጸም 75.82%፣ እርሻ ኢኮኖሚክስና ምርምር ሥርጭት 57.13%፤ በ2005 ዓ.ም የባዮቴክኖሎጂና ሰብል ጥበቃ 75.54%፣ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች 51.85%፤ በ2006 ዓ.ም ባዮ ቴክኖሎጂ ፕሮግራም 37.02% እና የሰብል ጥበቃ 70% ሲሆን አፈጻጸማቸው ከዕቅድ በታች መሆኑና ክትትል ተደርጎ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ ታውቋል፡፡ በሌላ መልኩ በመልካሳ የምርምር ማዕከል በ2006 ዓ.ም በምርምር የተገኙ የቦቆሎና ቦሎቄ ዘሮች ሳይተዋወቁ ወደ ምርት እንዲለወጡ ሳይደረግ የBreeder Seed በነቀዝ ተበልቶ መጥፋቱን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል::

105. በመልካሳ የምርምር ማዕከል የሚገኙ በተለያዩ የሥራ ሂደት ስር የሚገኙ ኬዝ ቲሞች ለስራ ማስኬጃ የሚያዝላቸው የበጀት ዕቅድ የሚሰራውን ስራ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ከእቅድ በላይ እንደተጠቀሙ ከ2004 ዓ.ም የካፒታል በጀት አጠቃቀም ለመረዳት ተችሏል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| የፕሮ ግራም ኮድ | ኬዝ ቲም | ለ2004 ዓ.ም የተመደበ በጀት | እስከ አራተኛው ሩብ ዓመት ሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት በመብለጥ |
|---|---|---|---|---|
| 1-1 | የአገዳና ብዕር ሰብሎች | 691,269.00 | 960,317.84 | (269,048.84) 39% |
| 1-2 | ጥራጥሬ፣ | 548,160.00 | 577,624.37 | (29,464.37) 5.37% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የቅባትና ቃጫ ሰብሎች | | | |
| 3-15 | የመስኖ፣ጠፈፍና ውሃ ማቆር | 435,593.00 | 498,389.56 | (62,796.56) 14.4% |

106. ስለጉዳዩ የግብርና ምርመር መዕከላት የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ቡድኑ ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከግብርና ጽ/ቤቶች ጋር ተናቦ የመስራቱ ሁኔታ ክፍተት ያለበት መሆኑን፣ ሥራው ብዙ ባለ ድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ መሆኑን እና ባለው ውስን መኪኖች እና የሰው ኃይል የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማከናወን አለመቻሉን እንዲሁም በመልካሳ የሚመደበው በጀት በፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ በጀት ከአንዱ ወደ ሌላኛው አዘዋውረው የሚጠቀሙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ ቡድኑ ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ በዋናው መ/ቤትም ይሁን በማዕከላት በየዓመቱ ኮሚቴ ተቋቁሞ ክትትል የሚያደርግ መሆኑን ነገር ግን የመረጃ አያያዝ ችግር ካለ መስተካከል እንደሚኖርበት ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ እንስቲትዩቱ በምርምር ማዕከላቱ ስላካሄደው የዕቅድ ክትትልና ግምገማ አፈፃፀም የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

107. ኢንስቲትዩቱ የግብርና ምርምር ማዕከላት ተግባራትን መሰረት ያደረገ የዕቅድ ክትትልና ግምገማ አለማካሄዱና ግብረመልስ አለመሰጠቱ የምርምር ማዕከላት በዕቅድ የያዟቸውን ስራዎች ባግባቡ ስለመፈፀማቸው በመከታተል በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱና ውጤታማ እንዳሆኑ ያደርጋል፡፡ የግብርና ምርምር ማዕከላቱም በትክክለኛ ፍላጎትና ጥናት ላይ የተመሰረተ የዕቅድ አዘገጃጀት፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ባለመዘርጋታቸው በአፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት ወቅታዊ ማሻሻያ እንዳያደርጉና ዓላማቸውን እንዳያሳኩ ያደርጋል፡፡

## በኢንስቲትዩቱ የመደበኛና ካፒታል በጀት ተመድቦላቸው የግብርና ምርምር የሚያከናውኑ አካላት ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ሥርዓትን መኖሩን በተመለከተ፡-

108.በኢንስቲትዩቱ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ተመድቦላቸው የግብርና ምርምር የሚያከናውኑ አካላት በሩብ፣ በስድስት ወር እና በአመት

ለኢንስቲትዩቱ የዕቅድና የዕቅድ ክንውን እንዲሁም ፋይናንሽያል አፈጻጸም ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

109.በኢንስቲትዩቱ በጀት ተመድቦላቸው የምርምር ተግባራትን ሲያከናውኑ የቆዩ ከ41 እስከ 44 ለሚደርሱ ለክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ለ16 የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ተቋማት ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደውን በጀት ኢንስቲትዩቱ በየጊዜው እንዲወራረድ አለማድረጉንና እያስተላለፈ መቆየቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ በጀት መድቦላቸው የሚሰሩ አካላት የዕቅድ ክንውንና የፋይናንሻል አፈጻጸም ሪፖርት ተከታትሎ እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ከ1999 በጀት አመት እስከ ሚያዚያ 7ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ጠቅላላ ድምር ብር 108,722,241.00 ( አንድ መቶ ስምንት ሚሊዬን ሰባት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ አንድ) ተሰብሳቢ ሂሳብ ያልተሰበሰበ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡(ዝርዝሩ **በአባሪ-4** ተያይዞ ቀርቧል፡፡)

110.ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የክልል እና የፌዴራል ምርምር ማዕከላት እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በወቅቱ የፋይናንሽያል እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት የሚያዘጋጁ መሆኑንና ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚጠይቃቸው አካል ባለመኖሩ ሪፖርቱን እንደማያቀርቡ ገልፀዋል፡፡በሌላ መልኩ የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተጠቀሱት ተቋማት በወቅቱ ሪፖርት እንዲሰጡን የምንጠይቅበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑና ተጠያቂነት ባለመኖሩ የተፈጠረ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

111.ከኢንስቲትዩቱ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ተመድቦላቸው የግብርና ምርምር የሚያከናውኑ አካላት በሩብ፣ በስድስት ወር እና በአመት ለኢንስቲትዩቱ የፊዚካል እና ፋይናንሽያል አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ አለመደረጉ ገንዘቡ ለታቀደለት አላማ በትክክል ስለመዋሉ

ለማረጋገጥ የማያስችል ሲሆን በተቋማቱና በኢንስቲትዩቱ ተጠያቂነትን እንዳይሰፍን በማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለምዝበራ እንዲጋለጥ በር ይከፍታል፡፡

## በግብርና ምርምር ማዕከላት በምርምር ሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል በጥናት ላይ ተመስርቶ የተመደበ መሆኑን በተመለከተ፡-

112.ኢንስቲትዩቱ በግብርና ምርምር ማዕከላት የሚፈለገውን የሰው ሃይል ስብጥር በማጥናትና መዋቅር ሊዘጋጅ እንዲሁም በመዋቅሩ መሰረት የምርምር ማዕከላቱ የሚያካሄዱትን ምርምር መሰረት ባደረገ መልኩ በሰው ሃይል እንዲሟሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

113. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት 8ቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚፈለገው የተመራማሪ ብዛት እና የትምህርት ደረጃ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪና በሶስተኛ ዲግሪ የሚፈለገውን ስብጥርና ብዛት እንዲሁም የስልጠና ዓይነት ባገናዘበ ሁኔታ ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠንቶ የሚፈለገው የሰው ሃይል መዋቅር እንዳልተዘጋጀ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ የግብርና ምርምር ማዕከላት ለምርም ስራ የሚያስፈልጋቸውን ተመራማሪ በተገቢው ሙያዊና የትምህርት ደረጃ ስብጥር ያላሟሉ ሲሆን ከ10 የምርምር ማዕከላት ከፒኤች ዲ ደረጃ የሚገኙ ተመራማሪዎች በሶስት የምርምር ማዕከላት ብቻ በአማካኝ 13 ሲገኙ በቀሪዎቹ 7 የምርምር ማዕከላት አንድ ወይም ምንም የፒኤች ዲ ተመራማሪ እንደሌላቸው በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩት ማዕከላት የተመራማሪ ብዛት እና የትምህርት ደረጃ ማሳያ ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ማዕከል | ቢ.ኤስሲ/ቢ.ኤ/ ቢ.ኢ.ዲ | | ኤምቪ.ኤስሲ/ ኤምኤስሲ/ኤምኤ | | ዲቪ.ኤም | | ፒኤችዲ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | |
| ሆለታ | 48 | 15 | 55 | 11 | 4 | 0 | 15 | 2 | 150 |
| መልካሳ | 59 | 6 | 52 | 6 | 0 | 0 | 12 | 1 | 136 |
| ቁሉምሳ | 34 | 6 | 20 | 1 | 1 | 0 | 2 | 0 | 64 |
| ደ/ዘይት | 32 | 13 | 30 | 13 | 2 | 1 | 13 | 1 | 105 |
| አምቦ | 25 | 2 | 17 | 4 | 0 | 0 | 1 | 0 | 49 |
| ባኮ | 11 | 1 | 5 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 18 |
| አሶሳ | 36 | 2 | 8 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 46 |
| ወረር | 44 | 0 | 12 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 58 |
| ፓዌ | 40 | 2 | 13 | 0 | 2 | 0 | 0 | 0 | 57 |
| ጅማ | 67 | 3 | 28 | 2 | 0 | 0 | 3 | 0 | 103 |
| ድምር | 396 | 50 | 240 | 38 | 10 | 1 | 47 | 4 | 786 |

114.የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በየአመቱ ዕቅድ ሲያዝ ምን ያህል የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ አብሮ ከማቀድ ውጪ በየማዕከላቱ የሚያስፈልገው ዝርዝር የተመራማሪዎች ብዛትና የትምህርት ደረጃ የማይታወቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡በተመሳሳይ መልኩ ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የቢ.ፒአር ጥናት ያለ ቢሆንም ተግባራዊነቱ በመላላቱ የተጠቀሱት ችግሮች መከሰታቸውን ገልጸዋል፡፡

115.በኢንስቲትዩቱ በግብርና ምርምር ማዕከላት የሚያስፈልጉትን ተመራማሪዎች የሙያ አይነትና የትምህርት ደረጃ ስብጥር ማለትም በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪና በሶስተኛ ዲግሪ ለይቶ መዋቅርና ጥናት በማካሄድ ተመራማሪዎች እንዲሟሉ ባለመደረጉ አብዛኞዎቹ የግብርና ምርምር ማዕከላት በሚያስፈልጋቸው ብቃት ያላቸው ተመራማሪዎችን ያላሟሉና የትምህርት ደረጃ ስብጥሩም በተለይ ፒኤች ዲ ያላቸው ተመራማሪዎች በሁሉም የምርምር ማዕከላት በተመጣጣኝ መልኩ እንዳይሟሉ በማድረጉና የምርምር ስራው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዳይካሄድ አድርጓል፡፡

**በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ግዥዎች የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ መፈፀማቸውን በተመለከተ፡-**

116. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ለምርምር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ግዥ የተመራማሪዎችን ፍላጎትና መስፈርት (specification) መሰረት በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ የሌሎች ባለሙያዎችን አስተያየት በማገናዘብ በተመራማሪዎቹ የተጠየቁት ግዥዎች በወቅቱ ሊከናወኑ ይገባል፡፡

117. በኢንስቲትዩቱ የተከናወኑ ግዥዎች ማዕከላት በጠየቁት መስፈርት እንዲሁም የባለሙያዎችን አስተያየት መሰረት ባደረገ መልኩ በወቅቱ እንደማይቀርቡ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ስራ ኃላፊዎች በቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

118. ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች በማዕከላቱ ተመራማሪዎች ግዥ እንዲፈፀም ቢጠየቁም በወቅቱ ተገዝተው እንዲቀርቡ አለመደረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ ከማዕከላቱ ፍላጎት ውጪ በኢንስቲትዩቱ ተገዝተው የተላኩና በማዕከላቱ መጋዘን ውስጥ ያለ ስራ ለረጅም ዓመታት የቆዩ መሳሪያዎች (ቶነሮች፣ ኬሚካሎች፣ አካፋና ዶማዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች ወ.ዘ.ተ) መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የሜካናይዜሽን የሥራ ሂደት በግዥ ፍላጎት ላይ ከተቀመጠው እስፔስፊኬሽን ውጭ ማለትም ፍላት አይረን ጠይቆ ሺት ሜታል የተገዛለት መሆኑ እና ከደረጃ በታች የሆኑ በቀላሉ የሚታጠፉ/የሚበላሹ/ እስኩዌር ፓይፖች እንዲሁም በቲሹ ካልቸር ከደረጃ በታች የሆኑ እና የማይገጥሙ ዲስፖዘብል ጃሮች የላብራቶሪ ዕቃዎች ተገዝተው የቀረቡ መሆኑ ተገልፃል፡፡ በአሶሳ ግብርና ምርምር ማዕከል ግዥዎች ከግዥ ሰራተኛ ውጭ በተለያዩ ባለሞያዎች የሚፈፀሙ ሲሆን፣ ለምርምር ሥራ በተመራማሪዎች ከተጠየቀው መስፈርት ውጭ በብር 92,000 የተገዛ 10,000 ሜትር ገመድ በተጠየቀው መስፈርት መሰረት ባለመገዛቱ ያለ አገልግሎት መቀመጡን የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡ በአምቦ የግብርና ምርምር ማዕከል ተመሳሳይ ፕሪንተር ሳይኖር ከኢንስቲትዩቱ የተላኩ ቶነሮች እንዳሉ ታውቋል፡፡

በቂሊምሳ የግብርና ምርምር ማዕከልና በአካባቢው ደግሞ ሽንብራ በማይመረትበት አከባቢ ቢሆንም የሽንብራ መዝሪያ መሳሪያ ያለስራ ተቀምጦ እንደሚገኝ ለማየት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በመልካሳ የግብርና ምርምር ማዕከል 1.5 ሚሊዮን ብር ሊያወጡ የሚችሉ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች (አምፑሎች፣ ጋስኬቶች፣ ፍሬንቻዎች…) ከተፈለገው በላይ ተገዝተው ለብዙ አመታት ያለስራ በጆንያ ተቀምጠው ለአደጋ እየተጋለጡ ያሉበት ሁኔታ መኖሩን በኦዲቱ ወቅት በመስክ እይታ እና ከተከለሱት ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

119. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ግዥ የሚከናወነው በኢንስቲትዩቱ በመሆኑና የምርምር ማዕከላቱን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ የተፈፀሙ ባለመሆኑ ችግሩ ሊፈጠር መቻሉን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የኬሚካል ግዥዎች በአቅራቢዎች ችግር የተከሰቱ መሆኑና ከፍላጎት ውጪ የተገዙ ንብረቶችን በተመለከተ ደግሞ አሰራሩ ስህተት የነበረበት በመሆኑ መስተካከል እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

120. በኢንስቲትዩቱ ለግብርና ምርምር ማዕከላት አገልግሎት እንዲውሉ የሚከናወኑ ግዥዎች የየማዕከላቱ ተመራማሪዎች ለሚያካሂዱት ምርምር የሚያስፈልጓቸውን ግብዓቶች ፍላጎት መሰረት ባደረገ ወይም ባቀረቡት መስፈርት(specification) እና በባለ ሙያ አስተያየት የተመሰረተ አለመሆኑ የተገዙ ንብረቶች የማይፈለጉ ቦታዎች ላይ ተልከው ያለ አገልግሎት እንዲቆዩ እና ለብልሽት እንዲጋለጡ በማድረግ የመንግስት ሀብት ያለአግባብ እንዲባክን ከማድረጉም በላይ በኢንስቲትዩቱ የግዥ አሰራር ቁጠባን፣ ቅልጥፍናንና ተጠያቂነትን በሚያጠናክር መልኩ እንዳይካሄድ አድርጓል፡፡

## በኢንስቲትዩቱ የተገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀም እና አወጋገድን በተመለከተ፡-

121. ኢንስቲትዩቱ በዋናው መ/ቤት እና በሁሉም የግብርና ምርምር ማዕከላት ስራ ላይ ሊውል የሚችል የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ለምርምር ማዕከላቱ የተገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች፣ ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸውና የማይሰሩት ንብረቶች በአግባቡ ሊወገዱ ይገባል፡፡

122.በኦዲቱ ወቅት በተካሄደ የመስክ ጉብኝት፣ የዶክሜንት ክለሳና ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ተመርጠው በታዩት በስምንቱም የምርምር ማዕከላት የንብረት አያያዝ ሥርዓት እና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

123.በታዩት በስምንቱም የምርምር ማዕከላት በተለያዩ የንብረት ማስቀመጫ መጋዘኖችና ጋራዦች (እርሻ መሳሪያዎች ፣ኬሚካሎች፣ የተለያዩ ዘሮች፣…) ንብረቶች እንዲይዙ የሚደረጉ ባለሙያዎች ስለ ንብረት አያያዝና አጠባበቅ ተገቢውን ስልጠና እንዳልወሰዱ ታውቋል፡፡ በምርምር በማዕከላቱ ሥር የሚገኙ የተለያዩ ንብረቶች (የእርሻ መሳሪያዎች፣ የእርሻ ግብዓቶች፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች፣ ኬሚካሎች፣ ተሽከርካሪዎች እና ዘረ መሎች/germ plasm) በአግባቡ ተይዘው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማይደረግ ሲሆን ተጠግነው አገልግሎት ላይ የማይውሉ ንብረቶች በአግባቡ እንዲወገዱ እንዳልተደረጉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የላብራቶሪ ንብረቶች በትክክል ስለመስራታቸው የመለካት(calibrate) ሥራ አለመደረጉና ከተገዙ 10 ዓመት ያለፋቸው መሳሪየዎች አገልግሎት ሳይሰጡ በየማዕከላቱ የተቀመጡ መሆኑ ለምሳሌ፤- በአሶሳ የግብርና ምርምር ማዕከል ሁለት አፈር መፍጪያ (Soil Grinder)፣ የሴንተር ፋጋል መሳሪያ፣ የመስመር መዝሪያ (Row Planter)፣የመስመር ማውጫ (row maker)፣ የመሬት ማስተካከያ (land leveler)፣የውሃ መስመር (Irrigation pipe) እና መፈልፈያ መሳሪያዎች መኖራቸው፤ በባኮ የግብርና ምርምር ማዕከል ኦቨኖች፣ ግሮውዝ ቻምበር እና ስድስት የላብራቶሪ ሼልፎች፤ በአምቦ የግብርና ምርምር ማዕከል ደግሞ ያለ ክፍሉ ለብዙ አመት

የተቀመጠ እና አገልግሎት ያልሰጠ እስፔክትሮ ሜትር መሳሪያ እና ከ2004 ዓ.ም በፊት ተገዝተው የመጡ ሁለት ጂ ቪ ሲ ካሜራዎች እና ሶስት ቶነሮች፣ በቁሉምሳ የምርምር በማዕከል የማይፈለጉ ለረጅም ጊዜ የቆዩ የሸንብራ መዝሪያ መሳሪያ፣ አራት ትናንሽ መውቂያ መሳሪያዎች፣ ብዛት ያላቸው ጎግሎች እና ብዛታቸው 10 የሆኑ St. steel Word Furnace long በማዕከሉ የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን እና ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየ Growth Chamber መሳሪያ መኖሩ፤በመልካሳ የምርምር ማዕከል ስር የሚገኙ ሁለት የሐር መፍተያ ማሽኖች ለአምስት ዓመታት አገልግሎት ሳይሰጡ ከሚወገዱ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው በክምችት መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት በተካሄዱ የመስክ ጉብኝቶች፣ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡






**ፎቶ ቁጥር ሁለት በቁሉምሳ ለብክነት የተጋለጡ የማዳበሪያ ክምችት አቀማመጥ እና በመልካሳ አገልግሎት ሳይሰጡ ለረጅም ጊዜ የቆሙ የእርሻ መሳሪያዎች፤**

124.ከዚህ በተጨማሪ ለምርምር ማዕከላቱ አገልግሎት እንዲሰጡ ተገዝተው በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉና መወገድ የሚኖርባቸውን ንብረቶች በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው ግምገማ ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች በምርምር ማዕከላቱ ሳይወገዱ እንደተቀመጡ ለማወቅ ተችላል፡፡ በአሶሳ፣ በሆለታ፣ በቁሉምሳ እና በወረር የምርምር ማዕከላት የሚገኙ 22 ተሸከርካሪዎች መኖራቸው፤ በመልካሳ የምርምር ማዕከል 1.5 ሚሊዮን ብር ሊያወጡ የሚችሉ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች

(አምፑሎች፣ ጋስኬቶች፣ ፍሬንቻዎች...) በጆንያ ተቀምጠው ለሌላ አደጋ እየተጋለጡ ያሉበት ሁኔታ መኖሩን ፣ ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች በስምንቱም ማዕከላት ከሚፈለጉት ቁጥር በላይ ተከማችተው እንዲሁም የተበላሹ እና ያልተበላሹ ሳይለዩ በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ በሚችል መልኩ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን (ለምሳሌ፡-ብዙ ቁጥር ያላቸው እና የብልሽት ዘመናቸው ሳያልፍ ተጠቅሞ ለመጨረስ የማይቻሉ ETADA በመልካሳ የምርምር ማዕከል ቲሹ ካልቸር ላብራቶሪ መኖራቸውን፣ በማዕከሉ የማይፈለጉ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ነገር ግን ያልተበላሹ ኬሚካሎች መኖራቸውን(ኦዳ ሜታን፣ ቤንዞይክ አሲድ፣ ዲክሉኮስ፣ ይስት ኤክስትራክት...በቲሹ ካልቸር ላብራቶሪ)፣ በጋራዥ ክፍል የሚገኙ እና ብዙ ቁጥር ያላቸው ጌጆች፣ ችንጋዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች... በማዕከሉ የማይፈለጉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በተካሄደው የመስክ ጉብኝት እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከባለሙያዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡






**ፎቶ ቁጥር ሶስት በአሰሳ የሚገንኝ ኮልድ ሩም እና በወረር የሚገኝ ኮምባይነር ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ሲችሉ ከ 5 ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ የቆሙ፤**

125. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የንብረት አያያዝን በተመለከተ ለወደፊቱ በንብረት አያያዝ ዙሪያ ሥልጠና መሰጠት ያለበት መሆኑን እና የመጠለያ/የመጋዘን እጥረት በመኖሩ የተጠቀሱት ችግሮች መፈጠራቸውን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ተጠግነው አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶችን በተመለከተ ንብረቶችን ለማስጠገን

የባለሞያ እና የበጀት እጥረት በመኖሩ አለመከናወኑን፣ ኬሚካልን በተመለከተ ደግሞ የሚወገደው በአገር አቀፍ ደረጃ በመሆኑ ያልተከናወነ መሆኑ እና ሌሎች መወገድ የነበረባቸውን ንብረቶች ለኢንስቲትዩቱ እንዲያስወግድላቸው ማሳወቃቸውን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኬሚካልን ማስወገድ ከተቋሙ አቅም በላይ መሆኑን ገልፀው፣ ዘረ መሎች በአግባቡ መያዝ እንዳለባቸው እንደሚያምኑና በዋናው መ/ቤት እየተኬደበት ያለው የAccriditation ሥራ የንብረት አያያዝና ጥገናን ችግር ጭምር የሚፈታ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

126.በኢንስቲትዩቱ ለግብርና ምርምር ማዕከላቱ አገልግሎት እንዲሰጡ የተገዙ ንብረቶች /መሳሪያዎች/ እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ለመያዝ፣ስራ ላይ ለማዋልና ሊወገዱ የሚገባቸውን ንብረቶች ደግሞ ለማስወገድ የሚያስችል የንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ አለመዘጋጀቱና ስራ ላይ አለመዋሉ እንዲሁም የተጠቀሱት ንብረቶችን በአግባቡ አለመያዛቸው ንብረቶቹ ለብክነት እንዲጋለጡ በማድረግ በሰውና በአካባቢ ላይ ተጽኖ የሚያሳድሩ መሆኑ እንዲሁም ጊዜያቸው ያለፈባቸውና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ባለመወገዳቸው ንብረቶቹ ወደ ገንዘብ ተቀይረው ለሌላ አገልግሎት እንዳይውሉ ከማድረጉም በላይ የመጋዘን ጥበትን እና ለአካባቢ ደህንነት ስጋት በመፍጠር በምርምር ማዕከላቱ ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ስርዓት እንዳይኖር አድርጓል፡፡

## በኢንስቲትዩቱ ስር የሚገኙ ማዕከላት ከ2004- 2006 ዓ.ም ኦዲት የተከናወነ ስለመሆኑ፡-

127.ኢንስቲትዩቱ በስሩ የሚገኙ ማዕከላት ላይ ኦዲት በማከናወን የውስጥ ቁጥጥሩ እንዲጠናከር ሊያደርግ እና በኦዲቱ ወቅት በተለዩ የአሰራር ግድፈቶች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

128.በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 ማዕከላት በሁለት ማዕከላት ( አሶሳ እና ባኮ) ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለማዕከላቱ የተመደበ ቢሆንም የተመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም ማዕከላቱ ለተቋቋሙበት

አላማ ብቻ ማዋላቸውን የሚያመለክት የፋናንስ አፈጻጸም እና የኦዲት ሪፖርት እንዲሁም በኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት ስለተወሰደው የማስተካከያ እርምጃ የሚገልጽ ሰነድ በማዕከላት ደረጃ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሆለታ፣ ወረር እና ቁሉምሳ የግብርና ምርምር ማዕከላት ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ኦዲት ስለመደረጋቸው የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

129. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ እና የግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ በማዕከላቱ የኦዲት ባለሙያዎች ባለመኖራቸው እና በኢንስቲትዩቱ የሚገኙ ኦዲተሮችም ብዛት ስለሌላቸው ኦዲቱ ሊከናወን አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

130. በኢንስቲትዩቱ ስር የሚገኙ ማዕከላት ኦዲት በማከናወን የውስጥ ቁጥጥሩ እንዲጠናከር ባለመደረጉ በአሰራር ወቅት በተለዩ ግድፈቶች ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዳይወሰድ የሚያደርግ መሆኑ እና የማዕከላቱ ሀብት ለብክነትና ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጡና በአሰራራቸውም ተጠያቂነት እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡

## የዘር እና ተረፈ ምርት ሽያጭ ውጤታማነትን በተመለከተ፡-

131. የግብርና ምርምር ማዕከላት ከዘር ና ተረፈ ምርት ሽያጭ ገቢ ሲሰበስቡ ገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ ሊያደርጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ሊዘረጉ ይገባል፡፡

132. በኢንስቲትዩቱ በህዳር 1999 ዓ.ም (እ/ም/እመ 79/1998) የወጣ የሽያጭ መመሪያ ቢኖርም በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩት ስምንቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት ከተረፈ ምርት የሚያገኙትን ገቢ አሰባሰብን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ ያላደረጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ያልዘረጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የተባዙ ዘሮች በወቅቱ ለሽያጭ ባለመቅረባቸው ለነቀዝ የተጋለጡ በማዕከላቱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ

ለሚመለከታቸው የምርምር ማዕከላቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ እና በመስክ በተደረገ ግምገማ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

133.በመልካሳ የግብርና ምርምር ማዕከል በ2006 ዓ.ም የተባዙ 721.03 ኩንታል የበቆሎ፣ ቦለቄ እና ጤፍ ዘሮች በወቅቱ እንዲሰራጩ ባለመደረጉ የተመረቱ ዘሮች ለነቀዝ እየተጋለጡ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በ2004/2005 ዓ.ም የምርት ዘመን 180 ኩንታል የሆነ የበቆሎ ዘር ለነቀዝ የተጋለጠ መሆኑ እንዲሁም የማሽላ ዘሮች በብዛት በነቀዝ በመጠቃታቸው ዘሩን ለማቆየት አስቸጋሪ ሁኔታ በባለሙያዎቹ ላይ የተፈጠረ መሆኑን ጉዳዩ አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከማዕከላቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቁሉምሳ የግብርና ምርምር ማዕከል 45.25 ኩንታል የሆነ የባቄላ ዘር ለነቀዝ የተጋለጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሆለታ የምርምር ማዕከል የተመረቱ 20 ኩንታል የባቄላ እና የአተር ዘር በነቀዝ ተበልቶ ከጥቅም ውጪ መሆኑንና በሁሉም ማዕከላት በሚካሄዱ የዘር ማባዛት ስራ የሚመረቱ ዘሮችን ለተባይና ለጉዳት ሳይጋለጡ ለማከማቸት የሚያስችሉ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች እንደሌሉ በኦዲቱ ወቅት በመስክ በተደረገ ግምገማ ለማወቅ ተችሏል፡፡




ፎቶ ቁጥር አራት በመልካሳ ለነቀዝ የተጋለጡ/የተጠቁ ቅድመ መስራች የማሽላ ዘሮች እና በሆለታ ለነቀዝ የተጋለጡ ባቄላና አተር ዘሮች፣

136. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የግብርና ምርምር ማዕከላት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሽያጭ መመሪያ መኖሩን የማያውቁና ከዚህ በፊት ሲከናወን በነበረበት ሁኔት በኮሚቴ ሽያጩን የሚያከናውኑ መሆኑን እንዲሁም ዘሮች ለነቀዝ ሊጋለጡ የቻሉበት ምክንያት የተሟላ መጋዘን ባለመኖሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መመሪያው ተከልሶ ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት እና የዘር አለመሰራጨቱ ችግር የተከሰተው ከፍላጎት ማጣት ጋር በተያያዘ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

137. የግብርና ምርምር ማዕከላት ከዘር ና ተረፈ ምርት ሽያጭ የሚያገኙትን ገቢ አሰባሰብን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ አለመደረጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ባለመዘርጋቱ እንዲሁም የተመረቱ የተለያዩ አይነት ዘሮች በወቅቱ ለአርሶ አደሮች በሽያጭ እንዲቀርቡ አለመደረጉ እና በምርምር ማዕከላቱ የሚካሄዱ ከዘርና ተረፈ ምርት ሽያጭ የሚሰበሰቡትን ገቢ ለብክነት እና ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጡ እና የውስጥ ገቢያቸው እንዲቀንስ ሊያደርግ እንዲሁም በምርምር ማዕከላቱ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች አለመኖር የተመረቱ ምርቶች ለተባይ አደጋ በማጋለጥ በማዕከላቱ የምርምር ዓላማ እንዳይሳካ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል እና እንስሳት ምርምር ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት የፌዴራል ግብርና ምርመር ማዕከላት የታዩት ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

138. በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 ማዕከላት (ሆለታ፣ ደብረ ዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ ወረር እና አሶሳ) በ6ቱ (ቁሉምሳ፣ ወረር፣ ሆለታ፣ አምቦ፣ ባኮና አሶሳ) ከአከባቢያቸው ስነ ምህዳር ጋር የሚጣጣሙ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት ሊውሉ የሚችሉ እና የግብርና የወጪ ምርትን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያግዙ የግብርና ምርቶች በምርምሮች ማዕከላቱ በእቅድ ተይዘውና ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው በሚፈለገው ደረጃ የማይከናወኑ መሆኑ፣
139. የቅባት እህሎች ጥራት ማሻሻያ ሙከራ አፈፃፀምን በመልካሳ፣ በሆለታ፣ በወረር፣ በቁልምሳና በቦኮ እና በአምቦ ማዕከላት የተካሄዱት ምርምሮች አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች አተገባበር የአቅም ውስንነት ያለበት መሆኑ፣
140. የቢራ ገብስን በጥራት ለማምረት የማያስችሉ ችግሮችና ቅድመ ሁኔታዎች መኖራቸው እነሱም ገብሱ በሚበቅልበት ወቅት አብሮ የሚበቅል የሲናር ችግር መኖር፣ ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተዘራው ዘሮች ከሌላ ዝርያ ጋር የተቀላቀሉ በመሆናቸው አርሶ አደሮች ያመረቱት የቢራ ገብስ ጥራቱን ያልጠበቀ እንዲሆን በማድረጉ አርሶ አደሮች ካመረቱት ምርት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው መሆኑ፣
141. በባቄላ፣ በአኩሪ አተር እና አተርን ጥራት ባለው መልኩ ለማምረት የሚያስችሉ ለዋግ፣ የትል እና የአረም መድሃኒት ለመጠቀም የሚያስችሉ ጥናቶች እና

የምርምር ውጤቶች በምርምር ማዕከላቱ ተከናውነው ለተግባራዊነት ወደ አርሶ አደሩ ያልደረሱ መሆኑ፣

142.በግብርና ምርምር ማዕከላቱ በተወሰነ ደረጃ በሚካሄዱ የቫይታሚንና የፕሮቲን ከፍተኛ ይዘት ያላቸውን የበቆሎና የስንዴ ዝርያዎች ውጤትን በግንዛቤ ማነስ ችግር ያልተጠቀሙበት መሆኑ ፣

143.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት (ሆለታ፣ ደብረ ዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ ወረር እና አሶሳ) በፌዴራል ግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ትስስርና ተግባቢነት የሌለ መሆኑ፣

144. በማዕከላቱ የሚከናወኑ የምርምር ውጤቶችን በግብርና ኤክስቴንሽን እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየጊዜው በተከታታይነት የማያሳውቁ መሆኑን፣

145. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በፌዴራልና ክልል ምርምር ማዕከላት በመሰረታዊ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዙሪያ፣ የማንጎ አመራረትና ድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ፣ የወተት ከብት እርባታ ዘዴ፣ የበግና ፍየል ዕርባታ ሥልጠና፣ የሰሊጥ የተሻሻሉ አሰራሮች፣ በዶሮ እርባታ ላይ የተሰሩ ሥራዎች፤ዘመናዊ የበግና የፍየል ማድለብ ሥራ ሥልጠና እና የማንዋል ዝግጅት፤የእንስሳት መኖ እና አመጋገብ ዘዴ፤ቆዳና ሌጦን በአግባቡ የማምረት እና የመያዝ እንዲሁም ወደ ገበያ ማቅረብ ዘዴ የሥልጠና ማንዋል ዝግጅት፤የተሻሻሉ የንብ እርባታ ዘዴ፤ በስንዴ ዝርያ የማላመድ፣ በበቆሎና በተባይ መከላከል ዙሪያ በተደጋጋሚ/ በተመሳሳይ ወቅት እና ጊዜ ያለቅንጅት/ የተሰሩ/እየተሰሩ ያሉ የምርምር ተግባራት መሆናቸው፣

146. በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

147. በማዕከላቱ ሥር የሚገኙ የተለያዩ የምርምር ዘርፍ ላብራቶሪዎች የሚሠሩትን ሥራ አቀናጅተው የማይተገብሩ እና በአንዱ ዘርፍ ያለውን ላብራቶሪ ያለውን ዕቃ/ኬሚካል ሌላኛው ዘርፍ የማያውቀው መሆኑ፣

148. በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

149. በሁሉም ማዕከላት በሰብልና በእንስሳት ዘርፎች በሚካሄዱ ምርምሮች አንዱ ምርምር ለሌላው የምርምር አይነት ግብአት እንዲሆን የሚያስችል ማለትም የኮምፖስት ሥራ፣ የከብት መኖን ከሌሎች ሰብሎች ጋር በማፈራረቅ፣ ለእንስሳት መኖ በማዋል ውጤታማ ሥራዎች የማይሰሩ መሆኑ፣ በቡድን ሊከናወኑ የሚችሉ የምርምር ስራዎችን በቡድን የማይሰሩ በመሆኑ አንድ ሰራተኛ ሥራ በሚለቅበት ወቅት ሌላው ሰራተኛ የተጀመሩ ተግባራትን ማስቀጠል ያልተቻለ መሆኑ፣

150. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች (ወረር፣ ጅጅጋ እና አሶሳ) የእንስሳት ሃብት ልማት፣ የእንስሳት መኖና ምግብ የማምረትና የማሻሻል ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ አለመሆኑ፣

151. በእነዚህ አካባቢዎች የእንስሳት ዘርፍ ላብራቶሪ እንዲኖር አለመደረጉ፣ የእንስሳት ቴክኖሎጂ ሥርጭቱ ደካማ መሆኑ፣ የተሻሻሉ የወተት ከብት ዝርያዎች አቅርቦት አለመኖሩን፣

152. የሲንክሮናይዜሽን (የኮርማና የጊደር ፍላጎት የማጣጣም ሥራ) ውጤታማ በማድረግ ተጠቃሚው ጋር እንዲደርስ ያልተደረገ መሆኑ፣

153. በቤንሻንጉል ክልል የእንስሳት እርባታ ስብጥር ወደ 47 በመቶ የሚወክሉት ፍየሎች መሆናቸውን መረጃዎች የሚያመለክቱ ቢሆንም በፍየሎች እና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ምርምር ያልተደረገ መሆኑ እና በንብ በሽታ እና በዶሮ እርባታ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ያልተደረገ መሆኑ፣

154. በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱ ማዕከላት በሰብል እና በእንስሳት ዙሪያ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠርና ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ያልተከናወነ መሆኑ፣

155. በመልካሳ እና ቁሉምሳ የገበያ ትስስር ጥናቱ ባለመከናወኑ ድንች፣ ሽንኩርት እና ቲማቲም በአከባቢው በስፋት የሚመረት ቢሆንም የገበያ ችግር ያለባቸው መሆኑና በሆለታ በሰብል ዘርፍ ኑግ እና ተልባ ላይ አርሶ አደሩ ገበያ ላይ አቅርቦ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ያልተፈጠረ መሆኑ፣

156. በእንስሳት ዘርፍ ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኤጀሬ፣ ደንዲ፣ ወልመራ፣ ጀልዱ፣ ጥቁር እንጪኒ፣ አቡሽገ እና ቀቤና አከባቢ የመኖን ዘር እጥረት ለመቀነስ የተከናወኑ ተግባራት ቢኖሩም የተመረቱ ዘሮችን አርሶ አደሮች በመሸጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚያስችላቸው ሁኔታ ያልተፈጠረ መሆኑ፣

157.በወረር በሰብል ዘርፍ ሰሊጥ፣ ስንዴና በቆሎ እንዲሁም በእንስሳት ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የእንስሳት ተዋጽኦን አርብቶ አደሩ/ከፊል አርብቶ አደሩ ተጠቃሚ ሊሆኑ አለመቻላቸውን እንዲሁም በአሶሳ እና ባኮ አከባቢ አኩሪ አተር ለገበያ ቀርቦ ውጤታማ መሆን ያለመቻሉ፣

158.በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት በግብርና ምርምር የተዘጋጁ የተለያዩ ማንዋሎች እንዲሁም ፓኬጆች በአከባቢው ቋንቋ ተተርጉመው ለባለድርሻ አካላት እና ለአርሶ አደሮች እንዲሰራጭ ያልተደረገ መሆኑ፣

159.የተለያዩ ፓኬጆች እና የአሰራር ማንዋሎች በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ ብቻ የተዘጋጁ ሲሆን በሌላ ቋንቋ (በሶማሊኛ፣ በአፋርኛ፣ በኦሮሚኛ…) ተተርጉመው ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያልተደረገ መሆኑ፣

160. የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች የሚኖራቸውን ተጽኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና ሥርዓት እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል ምርምር መካሄድ እንዳለበት ሃገራዊ የግብርና ምርምር ፖሊሲና እስትራቴጂ የሚገልጽ ቢሆንም ያልተተገበረ መሆኑ፣

161. በናሙና ተመርጠው በታዩ የምርምር ማዕከላት (ሆለታ፣አምቦ፣ ባኮ፣ አሶሳ፣ ደብረዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳና ወረር) ማዕከላት የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት…) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል ጥናት ያልተከናወነ መሆኑ፣

162.በተጠቀሱት ማዕከላት ከፀረ ተባይ ኬሚካሎች አጠቃቀም ጋር የተያያዘ የግንዛቤ ችግሮችን ለመቅረፍ የተሰሩ ስራዎች ባለመኖራቸው የአከባቢው ህብረተሰብ ኬሚካል የመጣባቸውን እቃዎችና በርሜሎች ለተለያዩ አገልግሎቶች (ለጋዝ፣ ለዘይት፣ ለውሃ…) የሚጠቀሙበት መሆኑ፣

163. በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተሰጡ ሥልጠናዎች በሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ውስጥ አፈጻጸማቸው ከዕቅድ ጋር ተነጻጸሮ የማይቀርብ መሆኑ፣ ሥልጠናዎች

የሚለኩበት ወጥ የሆነ የመከታተያ ሥርዓት አለመኖሩ እና ግብረመልስ የማይሰጡ መሆኑ፣

164. በቁሉምሳ በ2006 ዓ.ም በእንስሳት ምርምር የሥራ ሂደት የታቀደ ሥልጠናው ለሌላ ጊዜ የተላለፈ መሆኑን፣ በአሶሳ በኩይሳ አርሶ አደሮች ለስልጠና ተመዝግበው በወቅቱ ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ እና በወረር በበግ፣ በፍየል፣ በስንዴ፣ በሰሊጥ፣ በመኖ ዘሮች እንዲሁም በማዳቀል ሥራ ዙሪያ ሥልጠና የተሰጣቸው ቢሆንም ግብረመልስ ያልተሰጠ መሆኑን፣

165. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ ማዕከላት የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ ማዕከል (Implementing Center) ሆነው የተመረጡበትን መስፈርት የሚያሳይ ሰነድ ማግኘት አለመቻሉን እና የልቀት ማዕከላቱ ስነ ምህዳርን፣ የህብረተሰቡን አመራረት ሁኔታ፣ የማዕከላቱን ማስፈጸም አቅም ወ.ዘ.ተ መሰረት አድርገው ያልተመረጡ መሆኑ፣

166. የማንጎ ምርት በስፋት በአሶሳ ያለ መሆኑን ማስረጃዎች የሚያመለክቱ ቢሆንም ማስተባበሪያው መልካሳ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም ከእንስሳት ጋር በተያያዘ ለአርብቶ አደሩ እና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ የልቀት ማዕከል የሌለ መሆኑ፣

167. በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት የምርምር ስራዎች ተግባራዊ እና ተግባራዊ ያልሆኑ እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውጤት ሊሰጡ የሚችሉና የማይችሉ ተብለው ተለይተው በዕቅድ እንዲያዙ የማይደረጉ እና አፈጻጸማቸውም በዚሁ መልክ የማይቀርቡ መሆኑ፣

168. በእንስሳት ዘርፍ የሚያዙ ዕቅዶች አብዛኛዎቹ በረጅም ጊዜ ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸው እና በእንስሳት ዘርፍ በነባር ዝርያዎች ላይ የሚደረገው ምርምር ሥራ ውስን መሆኑ፣

169. እያንዳንዱ ቴክኖሎጂዎች ከቀረበ/ከተሰራጨ በኋላ ቴክኖሎጂዎቹን ወጪያቸውን መቀነስ እና በስፋት የማዳረስ ተግባር በማዕከላቱ አለመከናወኑን፣

170. የመሬትን ለምነት ሊጠብቁ እና የፀረ- አረም ወጪን መቀነስ የሚችሉ (ኮምፖስት፣ ቬርሚ ኮምፖስት፣ አረምን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን በማፍለቅ…) ቴክኖሎጂዎችን በስፋት በማሰራጨት አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አለመደረጉ፣

171.ለግብርና ምርምር የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግሮች የማይነሱ እና የባለድርሻ አካላትን ስምምነት እንዲያገኙ የማይደረግ መሆኑ፣

172.በቁሉምሳ በእንስሳት እርባታ/ዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ፣ በተፈጥሮ ግጦሽ ማሻሻያ ዘዴ፣ በእንስሳት መኖ ችግሮች ላይ፣ በእንስሳት ተዋጽኦ፣ በእንስሳት ጤና፣ በበቆሎ ዘር ዙሪያ ፤ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የጥቁር አፈር ምርታማነት መቀነስን፤ የጉራጌ ዞን የአፈር ኮምጣጣነትን (Soil Acidity) ፣ በስምንት ወረዳዎች ላይ ውርጭ የተከሰተ መሆኑን እና በስልጤ ዞን የአፈር ለምነት እና የማዳበሪያ አጠቃቀም ችግርን፤በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የስንዴ ዝርያዎች በዋግ በሽታ መመታት፣ ሙሎ ወረዳ አከባቢ ንቦችን ሚለቅሙ ወፎች መኖራቸና የጤፍ በመስመር መዝራት ሥራ አድካሚነትን፣ በዞኑ የሚገኙ የልማት አካላት ግንኙነት ደካማ መሆኑ፤ በአምቦ የእንስሳት በሽታ፣ የበርበሬ ቫይራል በሽታ እና የማንጎ በሽታ (White scale mango)፤ በወረር በእንስሳት እርባታ/ዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ፣ በተፈጥሮ ግጦሽ ማሻሻያ ዘዴ፣ በእንስሳት መኖ ችግሮች ላይ፣ በእንስሳት ተዋጽኦ፣ በእንስሳት ጤና፣ በበቆሎ ዘር ዙሪያ ችግሮች መኖራቸው የተገለጹ ቢሆኑም እነኚህን ችግሮች ከመፍታት አንጻር የተሰራው ሥራ በጣም አነስተኛ መሆኑን፣

173.በመልካሳ አከባቢ አርሶ አደሮች የእርሻ መሳሪያ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ በተደጋጋሚ ቢገልፁም (የቢቢኤም ብዜት፣ የጤፍ መውቂያ፣ የመኖ መከርተፊያና የፓፓያ ማውረጃ፣ የበቆሎ መፈልፈያ፣ የጤፍ መውቂያ መሳሪያ) የእርሻ መሣሪያዎች በማምረት ችግሮቹ እንዲፈቱ ያልተደረገ መሆኑ፣

174.የግብርና ምርምር የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ላይ በማተኮር መስፈርት ወጥቶላቸው የተመረጡ አለመሆናቸው ማለትም የሥርዓተ ፆታን፣ አረጋውያንን፣ ወጣቶችንና ኤች. አይ ቪንና የመሳሰሉትን ያካተቱ ወይም ለነዚህ አካላት የሚውል የቴክኖሎጂ ውጤት እንዲኖር አለመደረጉ፣

175.የምርምር የመፍትሄ ሀሳቦች የተሻሉትን ለመምረጥ የሚያስችል ተገቢውን መስፈርት ማለትም የችግሩን አንገብጋቢነት፣ ተቋሚዊ የማስፈፀም አቅም ያገናዘበ መፍትሄ በማውጣት ትኩረት የሚደረግባቸው የምርምር ጉዳዮች ተለይተው በማስረጃነት የተያዙበት አግባብ ያለመኖሩ፣

176.በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የቀረቡ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ እና በግብርና ሥራ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ተብሎ ተለይቶ የተሰራጨ ቴክኖሎጂ አለመኖሩን፣

177.በናሙና ተመርጠው በታዩት በስምንቱም ማዕከላት ወደአገር ውስጥ የገባው ቴክኖሎጂ በኳራንቲን ቆይቶ የጤና ክትትል የተደረገለት እና ከበሽታ ነጻ መሆኑን የሚያመለክት ሪፖርት በማስረጃነት ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ፣

178.በማዕከላቱ ኳራንቲን በማቆየት ፍተሻ የማድረጉ ሥራ የላላ/ውስንነት ያለበት መሆኑ በዚህም ምክንያት በመልካሳ አከባቢ በአገራችን ያልተለመዱ ተባዮችና በሽታዎች ገብተው ጉዳት ያስከተሉበት ሁኔታ መኖሩ፣

179.በወረር ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከውጭ የሚመጡ ዝርያዎችና ቴክኖሎጂዎች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው ባለመግባታቸው የጥጥ ዝርያዎች፣ የቲማቲም ቦርቧሪ በሽታዎች መከሰታቸው እና በተጠቃሚዎች ላይ ጉዳትና ኪሳራ ያስከተሉ መሆኑን፣

180.በታዩት ስምንቱም ማዕከሎች እንዲከናወኑ የተደረጉ የምርምር ተግባራት በጥልቀት የሚፈጁት የገንዘብ መጠን ተተምኖ ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ አለመቅረቡን ፣ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት አጠቃላይ የፈጁት ወጪ እና ጊዜ ከዕቅዱ ጋር ተነጻጽሮ በማስረጃ አለመቅረቡን እና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፣

181.በወረር እና በአሶሳ ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸውና ከሶስት አመት በፊት ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የነበረባቸው በማዕከሉ የሚገኙ ህንጻዎች አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲሁም አገልግሎት መስጠት ሳይጀምሩ ለመፍረስ፣ ለመሰነጣጠቅ… እየተዳረጉ መሆኑን፣

182.በወረር የግብርና ምርምር ማዕከል የሚገኝ የፓንፕ ሳይት ግንባታ በጥናት ላይ ተመስርቶ የተገነባ ባለመሆኑ ከ2003-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 2,000,000 ብር (ሁለት ሚሊዮን ብር) ወጪ ተደርጎበት በ2006 ዓ.ም ግንባታው እንዲቋረጥ የተደረገ መሆኑ፣

183.ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩት የምርምር ማዕከላት ውስጥ በአራቱ ማዕከላት (በሆለታ፣ መልካሳ፣ ወረርና ቁሉምሳ) ብቻ 63 የምርምር ተግባራት እንዲቋረጡ መደረጉ፣

184.በአምቦ እየተካሄዱ የነበሩ ሶስት የግብርና ተግባራት (Activities) እንዲዘገዩ መደረጉን ፣ በአሶሳ በማዕከሉ በሰብል እና እንስሳት ዘርፎች የሚቀርቡ የምርምር ውጤቶች አቅርቦት መዘግየት የሚታይባቸው መሆኑ፣

185.በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱን የግብርና ምርምር ማዕከላት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ/ የሚካሄዱ ምርምሮች ፣ በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት እና በምርምር ሥራ ላይ የተሰማራ/ የሚሰማራ ማንኛውም አካል ተመዝግበው በኢንስቲትዩቱ በማዕከላዊነት ተይዘው መረጃዎቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ፣

186.እንዲሁም ከ2004 -2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ 17ቱም ማዕከላት ያወጡትን የምርምር ውጤቶች ማስረጃ በማዕከላዊነት በኢንስቲትዩቱ እና በየማዕከላቱ ተጠናቅሮ ያልተቀመጠ መሆኑን፣

187.ኢንስቲትዩቱ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ ስምንቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት የዕቅድ አፈጻጸም ሂደት በታቀደው መሰረት መሆኑንና የሚጠበቀውንም ውጤት ከያዘው ግብ አንጻር ክትትልና ግምገማ የሚከናወን ያለመሆኑ፣

188.በግብርና ምርምር ማዕከላቱ ለአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ለሙከራ የሚሰራጨው ዘር ከመዝራት እስከ አጭዶ ሰብስቦ ማስገባት ደረስ ያለው ሂደት የክትትልና ቁጥጥር ሥራ አነስተኛ መሆኑ፣

189.በማዕከላቱ ለአከባቢው ለግለሰብ የሚሸጠው ዘር ግለሰቡ ያለው መሬት ሳይጣራ የሚሸጥላቸው በመሆኑ ግለሰቦች መልሰው ለአርሶ አደሩ በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጡበት ሁኔታ መኖሩ፣

190.በማዕከላቱ አከባቢ ድንገት የሚከሰቱ ሁኔታዎችን (Emerging issues) /የመኖ እጥረት፣ የተባይና በሽታ ክስተት…/ ተከታትሎ የአርሶ አደር፣ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩን ችግር ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ያለመኖሩ፣

191.በወረር አሚባራ ወረዳ በ2006 ዓ.ም የጥጥ ላብራቶሪ ሥራ የቆመ መሆኑ እና ተከታትሎ የማስቀጠል ስራ አለመሰራቱ፣

192. በ2004 ዓ.ም በማዕከሉ የተባዙ የመኖ ዝርያዎች (ሮደስ፣ ፓኒከም፣ሲንክረስ/በፍል፣ ዝሆን ሳር፣ አልፋ አልፋ፣ ላብላብ፣ ለም አተር፣ ሰስባኒያና ሉኪኒያ) 20.2 ኩንታል ዘር የተባዛ መሆኑ፣ በ2005 ዓ.ም 15 ኩንታል ታቅዶ 8.3 ኩንታል የተባዛ መሆኑ፣ በ2004 ዓ.ም የዝሆን ሳር 50,000 (አምሳ ሺ) ቁርጥራጭ የተባዛ መሆኑ፣ እንዲሁም በ2005 ዓ.ም የስንዴ (ደንደአ፣ ሽሪማ፣ ህዳሴ-5595 ፣አጎልቾ-5520፣ ዲገሉ፣ ቀቀባ እና ጋአምቦ) 278.45 ኩንታል የተባዛ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ለአርብቶ አደሩ እና ለከፊል አርብቶ አደሩ እንዲሰራጭ እና ጥቅም ላይ እንዲውል አለመደረጉ፣

193. በመልካሳ ማዕከል በ2004 ዓ.ም ዕቅዱ ከአፈጻጸሙ ጋር ሲነጻጸር የባዮቴክኖሎጂ ሰብል ጥበቃ አፈጻጸም 75.82%፣ እርሻ ኢኮኖሚክስና ምርምር ሥርጭት 57.13%፤ በ2005 ዓ.ም የባዮቴክኖሎጂና ሰብል ጥበቃ 75.54%፣ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች 51.85%፤ በ2006 ዓ.ም ባዮ ቴክኖሎጂ ፕሮግራም 37.02% እና የሰብል ጥበቃ 70% ሲሆን አፈጻጸማቸው ከዕቅድ በታች መሆኑና ክትትል ተደርጎ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፣

194. በመልካሳ በ2006 ዓ.ም የቦቆሎና ቦሎቄ ዘሮች ተዋውቀው ሳያልቁን ወደ ምርት እንዲለወጡ ሳይደረግ የBreeder Seed በነቀዝ ተበልቶ ከማዕከሉ የጠፋ መሆኑ፣

195. በመልካሳ የምርምር ማዕከል የሚገኙ በተለያዩ የሥራ ሂደት ስር የሚገኙ ኬዝ ቲሞች የበጀት ዕቅድ የሚሰራውን ስራ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ፣

196. በኢንስቲትዩቱ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ተመድቦላቸው የግብርና ምርምር የሚያከናውኑ አካላት በሩብ፣ በስድስት ወር እና በአመት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ የዕቅድና የዕቅድ ክንውን እንዲሁም ፋይናንሽያል አፈጻጸም ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፣

197. በኢንስቲትዩቱ በጀት ተመድቦላቸው የምርምር ተግባራትን ሲያከናውኑ የቆዩ ከ41 እስከ 44 ለሚደርሱ ለክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ለ16 የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ተቋማት ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደውን በጀት በየጊዜው እንዲወራረድ ሳያደርግ እያስተላለፈ መቆየቱ እንዲሁም የዕቅድ ክንውንና የፋይናንሻል አፈጻጸም ሪፖርት ተከታትሎ እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ሥርዓት ባለመኖሩ ከ1999 በጀት አመት እስከ ሚያዚያ 7ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ጠቅላላ ድምር ብር

108,722,241.00 ( አንድ መቶ ስምንት ሚሊዬን ሰባት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ አንድ) ተሰብሳቢ ሂሳብ ያልተሰበሰበ መሆኑን፣

198. በናሙና ተመርጠው በታዩት 8ቱም የምርምር ማዕከላት በየማዕከላቱ የሚፈለገው የተመራማሪ ብዛት እና የትምህርት ደረጃ (የቢኤስሲ/ቢኤ/ቢኢዲ፣ ኤም ቪ ኤስሲ/ኤምኤስ ሲ/ኤም ኤ፣ዲቪ ኤም እና ፒ ኤች ዲ) ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠንቶ የሚፈለገው የሰው ሃይል ስብጥር መዋቅር ያልተሰራ መሆኑ በዚህም ምክንያት የፒኤችዲ ያላቸው ተመራማሪዎች በአንድ ማዕከል ላይ በብዛት ተመድበው እየሰሩ የሚገኙ መሆኑ፣

199.በኢንስቲትዩቱ የተከናወኑ ግዥዎች በወቅቱና ማዕከላት በጠየቁት መስፈርት እንዲሁም በባለሙያ አስተያየት መሰረት የሚከናወኑ አለመሆኑ፣

200.ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች በማዕከላቱ ግዥ እንዲፈፀም ቢጠየቁም በወቅቱ ተገዝተው እንዲቀርቡ አለመደረጋቸውን፣

201.ከማዕከላቱ ፍላጎት ውጪ በኢንስቲትዩቱ ተገዝተው የተላኩና በማዕከላቱ መጋዘን ውስጥ ለረጅም ዓመታት የቆዩ መሳሪያዎች (ቶነሮች፣ ኬሚካሎች፣ አካፋና ዶማዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች ወ.ዘ.ተ) መኖራቸው፣

202.የሜካናይዜሽን የሥራ ሂደት ከተቀመጠው እስፔስፊኬሽን ውጭ ማለትም ፋላት አይረን ጠይቆ ሺት ሜታል የተገዛለት መሆኑ እና ከደረጃ በታች የሆኑ በቀላሉ የሚታጠፉ/የሚበላሹ/ እስኩዌር ፓይፖች እንዲሁም በቲሹ ካልቸር ከደረጃ በታች የሆኑ እና የማይገጥሙ ዲስፖዘብል ጃሮች የላብራቶሪ ዕቃዎች ተገዝተው የቀረቡ መሆኑ፣

203.በአሶሳ ማዕከል ግዥዎች ከግዥ ሰራተኛ ውጭ በተለያዩ ባለሞያዎች የሚፈፀሙ መሆኑ፣ ለምርምር ሥራ በብር 92,000 የተገዛ 10,000 ሜትር ገመድ የተጠየቀው መስፈርት መሰረት ባለመገዛቱ ያለ አገልግሎት መቀመጡ፣

204.በአምቦ ማዕከል ተመሳሳይ ፕሪንተር ሳይኖር ከኢንስቲትዩቱ የተላኩ ቶነሮች መኖራቸው፣ ሽንብራ በማይመረትበት አከባቢ (በቁሉምሳ) የሽንብራ መዝሪያ መሳሪያ ተቀምጦ መገኘቱ እንዲሁም በመልካሳ ማዕከል 1.5 ሚሊዮን ብር ሊያወጣ የሚችል የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች (አምፑሎች፣ ጋስኬቶች፣

ፍሬንቻዎች...) ከተፈለገው በላይ ተገዝቶ ለብዙ አመታት በጆንያ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣

205.በኢንስቲትዩቱ የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጁ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ እንዲሁም የተገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያልተደረገ መሆኑ፣

206.በናሙና ተመርጠው በታዩት በስምንቱም የምርምር ማዕከላት የንብረት አያያዝ ሥርዓት እና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉን፣

207.በማዕከላቱ በተለያዩ ማከማቻዎች (እርሻ መሳሪያዎች ፣ኬሚካሎች፣ የተለያዩ ዘሮች፣ጋራገሮች...) ንብረት እንዲይዙ የሚደረጉ ባለሙያዎች ስለ ንብረት አያያዙ ዕውቀት የሌላቸው መሆኑ፣

208.በማዕከላቱ ሥር የሚገኙ ንብረቶች (የእርሻ መሳሪያዎች፣ የእርሻ ግብዐቶች፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች፣ ኬሚካሎች፣ ተሽከርካሪዎች እና ዘረ መሎች/germ plasm) በአግባቡ ተይዘው ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጋቸው፣ ተጠግነው አገልግሎት ላይ የማይውሉ ንብረቶች በአግባቡ እንዲወገዱ አለመደረጋቸው፣ የላብራቶሪ ንብረቶች በትክክል ስለመስራታቸው መለካት(calibrate) አለመደረጋቸው፣ እና

209.ከተገዙ 10 ዓመት ያለፋቸው መሳሪየዎች በአሶሳ ሁለት አፈር መፍጨ.ያ (Soil Grinder)፣ የሴንተር ፉጋል መሳሪያ፣ የመስመር መዝሪያ (Row Planter)፣የመስመር ማውጫ (row maker)፣ የመሬት ማስተካከያ (land leveler)፣የውሃ መስመር (Irrigation pipe) እና መፈልፈያ፤ በባኮ አቨኖች፣ ግሮውዝ ቻምበር እና ስድስት የላብራቶሪ ሼልፎች፣ አገልግሎት ሳይሰጡ በየማዕከሉ የተቀመጡ መሆኑ፣

210.በአምቦ ያለ ክፍሉ ለብዙ አመት የተቀመጠ እና አገልግሎት ያልሰጠ እስፔክትሮ ሜትር መሳሪያ እና ከ2004 ዓ.ም በፊት ተገዝቶ የመጡ ሁለት ጂ ቪ ሲ ካሜራዎች እና ሶስት ቶነሮች፣ አገልግሎት ሳይሰጡ በየማዕከሉ የተቀመጡ መሆኑ፣

211.በቁሉምሳ በማዕከሉ የማይፈለጉ ለረጅም ጊዜ የቆዩ የሸንብራ መዝሪያ መሳሪያ፣ አራት ትናንሽ መውቂያ መሳሪያዎች፣ ብዛት ያላቸው ጎግሎች እና ብዛታቸው 10

የሆኑ St. steel Word Furnace long በማዕከሉ የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን እና ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየ Growth Chamber መሳሪያ መኖሩ፣

212.በመልካሳ በማዕከሉ ስር የሚገኝ ሁለት የሐር መፍተያ ማሽን ለአምስት ዓመታት አገልግሎት ሳይሰጡ ከሚወገዱ ንብረቶች ጋር ተቀላቅሎ በክምችት መጋዘን ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣

213.እንዲሁም መወገድ የነበረባቸው ንብረቶች በ4ቱ ማዕከላት (አሶሳ፣ ሆለታ፣ ቁሉምሳ እና ወረር) የሚገኙ 22 ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ አለመደረጋቸውን፣

214.በመልካሳ በግምት 1.5 ሚሊዮን ብር ሊያወጣ የሚችል የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች (አምፑሎች፣ ጋስኬቶች፣ ፍሬንቻዎች…) በጆንያ ተቀምጠው ለሌላ አደጋ እየተጋለጡ ያሉበት ሁኔታ መኖሩን ፣

215. በስምንቱም ማዕከላት ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች ተከማችተው እንዲሁም የተበላሹ እና ያልተበላሹ ሳይለዩ በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ በሚችል መልኩ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን፣

216.በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 ማዕከላት በሁለት ማዕከላት (አሶሳ እና ባኮ) ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለማዕከሉ የመደበ ቢሆንም የተመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም ማዕከሉ ለተቋቋመበት አላማ ብቻ ማዋሉን የሚያመለክት የፋናንስ አፈጻጸም እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፣

217.በኢንስቲትዩቱ በህዳር 1999 ዓ.ም (እ/ም/እመ 79/1998) የወጣ የሽያጭ መመሪያ ቢኖርም በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት ከተረፈ ምርት የሚያገኙትን ገቢ አሰባሰብን ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ ያላደረጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ያልዘረጉ መሆኑ፣ እንዲሁም በማዕከላቱ የተባዙ ዘሮች በወቅቱ ባለመሰራጨታቸው (ለሽያጭ ባለመቅረባቸው) ለነቀዝ የተጋለጡ መሆኑ፣

218.በዘር ብዜት የተገኘ ዘር ሽያጭ በወቅቱ ባለመከናወኑ በመልካሳ በ2006 ዓ.ም የተባዙ 721.03 ኩንታል የበቆሎ፣ ቦለቄ እና ጤፍ ዘሮች ለነቀዝ እየተጋለጡ መሆኑ፣ በ2004/2005 ዓ.ም የምርት ዘመን 180 ኩንታል የሆነ በቆሎ ዘር ለነቀዝ

የተጋለጠ መሆኑ እንዲሁም የማሽላ ዘሮች በብዛት በነቀዝ በመጠቃታቸው ዘሩን ለማቆየት አስቸጋሪ ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑ፣

219. በቁሉምሳ 45.25 ኩንታል የሆነ የባቄላ ዘር ለነቀዝ የተጋለጠ መሆኑን፣

220. በሆለታ 20 ኩንታል ባቄላ እና አተር በነቀዝ ተበልቶ ከጥቅም ውጪ መሆኑ፣

221. በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት የዘር ብዜት ማከማቻ መጋዘን ደረጃውን ያልጠበቀ መሆኑ፣

ስለሆነም የግብርና ምርምር ቴክኖሎጂዎች በወቅቱ እና በጥራት ለአርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች እንዲቀርብ አለመደረጉ ሀገሪቷ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ወደ ኢንደስትሪው መር ለመምጣት ያቀደችውን ግብ በተሟላ መልኩ እንዳይሳካ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች እና ግድፈቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

222. የሀገራችን 85% አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ እንደ መሆኑ መጠን የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ከፍ እንዲል በማድረግ አርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለመጨመር እንዲሁም የግብርናው ዘርፍ ወደ ኢንዱስትሪው የሚሸጋገርበትን ሁኔታ የበለጠ ለማገዝ ለወደፊቱ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት ሊውሉ የሚችሉ የግብርና ምርቶች ላይ ምርምር መካሄድ አለበት፡፡

223. የግብርና ምርምር ውጤቶች እንዲስፋፉ ለማድረግ እና በአርሶ አደሩ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የምርምር ተግባራትን ለማከነወን እንዲቻል በፌዴራልግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ትስስርና ተግባቢነት ሊኖር ይገባል፡፡

224. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ የምርምር ተግባራት ውጤታማ እንዲሆኑ እንዲሁም ተግባራቱን ሳይቋረጡ ለማስቀጠል እንዲቻል ተመራማሪዎች ተግባራትን በቡድን ሊፈጽሙ እና በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

225. አገሪቷ ከፍተኛ የእንስሳት ኃብት ያላት በመሆኑ ይህን ያላትን የእንስሳት ኃብት ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ እና አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ በአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች የእንስሳት ሃብት ልማት፣ የእንስሳት መኖና ምግብ የማምረትና የማሻሻል ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት መሰራት አለበት፡፡

226.የግብርና ቴክኖሎጂዎችን አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች በገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በማምረት ጥራትና ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ ሸጠው ለመጠቀምና በዚህ ሂደት ገበያቸው በቀጣይነት እንዲያድግ ለማስቻል በሰብል እና በእንስሳት ዙሪያ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር እንዲሁም የህዝቡን ባህል ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶች ተከናውነው ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

227.አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች የምርምር ውጤቶችን መርጠው እንዲጠቀሙ እና ለማስፋፋት እንዲችሉ በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ የተለያዩ ማንዋሎች እንዲሁም ፓኬጆች በአከባቢው ቋንቋ ተተርጉመው ለባለድርሻ አካላት እና ለአርሶ አደሮች ሊሰራጩ ይገባል፡፡

228.የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት...) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል ጥናት ተጠንቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም ለተጠቃሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡

229. በአገራችን የሚከናወኑ የግብርና ምርቶች በአብዛኛው በዝናብ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ በወቅቱ አምርቶ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲችል ከግብርና ምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በወቅቱና በዕቅዳቸው መሰረት ሊከናወኑ እና የተጠቃሚውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የተሰጠው ሥልጠና በተግባር ስለመዋሉ ሊገመገም ይገባል፡፡

230.በአገራችን ሁሉንም በግብርናው ዘርፍ ተሰማርቶ የሚገኘውን የህብረተሰብ አካል ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል ማዕከላት የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Center) ሆነው ሲመረጡ በጥናት ወይም በመስፈርት ላይ ተመረኩዘው ሊመረጡ ይገባል፡፡

231.ጥራታቸውን የጠበቁ ቴክኖሎጂዎች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ ለአርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮቹ ለማሰራጨት እንዲቻል በግብርና መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮች ተግባራዊ ምርምር፣ በአጭር ጊዜ ውጤት

የሚሰጡና በአነስተኛ ወጪ ምርትን የሚያሳድጉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

232.የግብርና ምርምር ውጤቶችን አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ በስፋት እንዲሳተፍባቸው እና ውጤታማ ሊሆንባቸው የሚችልባቸውን የምርምር ውጤቶች በፍላጎቱ መሰረት መርጦ ለመጠቀም እንዲችል የሚካሄደው የግብርና ምርምርና የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግር የሚነሱ እና ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት መስፈርት ወጥቶላቸው መመረጥ ይኖርባቸዋል፡፡

233.በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ከአቅማቸው ጋር የሚመጣጠን ቴክኖሎጂ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

234.ወደ አገራችን የሚገቡ የግብርና ቴክኖሎጂዎች የተለያዩ በሽታዎችና ጸረ-ሰብል ነፍሳትን ይዘው እንዳይገቡ በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት የጤና ክትትል ከተደረገ በኋላ ቴክኖሎጂው ከበሽታ ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

235.ለኢንስቲትዩቱ የተመደበው ገንዘብ ለብክነት እንዳይዳረግ እንዲሁም ግንባታዎቹ በወቅቱ ተጠናቀው መስጠት የለባቸውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የሚከናወኑ ግንባታዎች፣ የምርምር ፕሮጀክቶች እና ተግባራት ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲጠናቀቁ ሊደረጉ፤ በማዕከላቱ እንዲከናወኑ የሚደረጉ ተግባራት በጥልቀት የሚፈጁት የገንዘብ መጠን ተተምኖ ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሊቀርቡ፤ እንዲሁም እያንዳንዱ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት አጠቃላይ የፈጁት ወጪ እና ጊዜ፣ መፍጀት ከነበረባቸው ጋር ተነጻጽሮ መቅረብ አለበት፡፡

236.የምርምር ውጤቶች ለሁሉም በግብርና ሥራ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች ለማስፋፋት እንዲሁም የድግግሞሽ ሥራን ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ/ የሚካሄዱ ምርምሮች ፣ በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት እና በምርምር ሥራ ላይ የተሰማራ/ የሚሰማራ ማንኛውም

አካል ተመዝግበው በኢንስቲትዩቱ በማዕከላዊነት ተይዘው መረጃዎቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

237.የግብርና ምርምር ውጤቶችን ወጥና ተከታታይ በሆነ መልኩ ለማስፋፋት እና ማዕከላቱን ውጤታማ ለማድረግ የምርምር ተግባራት የዕቅድ አፈጻጸሙ ሂደት በታቀደው መሰረት መሆኑንና የሚጠበቀውንም ውጤት በመጨረሻ ከማስመዝገብ አንጻር ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

238.ግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር እንዲሁም የሀብት ብክነት እንዳይኖር ለማስቻል የክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም 17ቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት ለኢንስቲትዩቱ የፋይናንሽያል እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

239.በሁሉም ማዕከላት የሚከናወኑ የምርምር ተግባራት ወጥ እና ተመጣጣኝ የሆነ ውጤት ማስገኘት እንዲችሉ በየማዕከላቱ የሚፈለገው የተመራማሪ ብዛት እና የትምህርት ደረጃ ተጠንቶ ሊታወቅ እና በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

240.የግዥ ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም ተገዝተው የቀረቡ ንብረቶች ለሌላ ብክነት ሳይጋለጡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለመድረግ እንዲቻል በኢንስቲትዩቱ የሚናወኑ ግዥዎች በወቅቱና በተጠየቀው መስፈርት እንዲሁም በባለሙያ አስተያየት መሰረት መሆን አለበት፡፡

241.የንብረት አያያዝ ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በኢንስቲትዩቱ የተገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊደረጉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸውና የማይሰሩት ሊወገዱ ይገባል፡፡

242.የተመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም ማዕከሉ ለተቋቋመበት አላማ ብቻ ማዋሉን ለማረጋገጥ በውስጥ ቁጥጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ክትትል ሊያደርጉ/ኦዲት ሊያከናውኑና በአሰራር ወቅት በተለዩ ግድፈቶች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

243. የግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር እንዲሁም ከውስጥ የሚሰበሰብውን ገቢ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሽያጭ መመሪያን

ተግባራዊ ሊያደርጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግተው ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በታዩ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የፌዴራልና ክልል ግብርና ምርምር ማዕከላት፣ የክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎችን በሙሉ በማቅረብ እና ለቀረቡ ቃለ-መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ለተደረገልን ትብብር ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች<br>/Issues/ | የመገምገሚያ መስፈርት<br>/Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. የአገሪቱን የግብርና ምርምር ቀልጣፋ፣ የተቀናጀ ውጤታማና በልማት ፍላጎት ላይ ያተኮረ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም አቅም መገንባቱን ማረጋገጥ፤ | 1. ለወደፊቱ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት ሊውሉ የሚችሉ የግብርና ምርቶች ላይ ምርምር ሊካሄድ ይገባል፡፡ |
| | 2. ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ጥራት ለማሻሻል አስፈላጊው ምርምር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3. የውጭ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግና፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለማላመድ፣ ለመጠቀምና ለማሰወገድ የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 4. በፌዴራልግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 5. በአርብቶ አደርና እርጥበት አጠር አከባቢዎች በእንስሳት ሃብት ልማት፣ በእንስሳት መኖና በምግብ የማምረትና የማሻሻል ዙሪያ ቴክኖሎጂዎችን ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 6. በእንስሳት ሃብት ልማት ሥራ ላይ ላልተማረው አርሶ አደርም፣ ተምሮ የግብርና ሥልጠና ለወሰደው አርሶ አደርም የሚሆኑ ከደረጃቸው ጋር የሚመጥኑ ፓኬጆች/ ቴክኖሎጂዎችን መዘጋጀትና በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | 7. በአርብቶ አደሩ አከባቢ ከጎሳ መሪዎች የህዝብ ተመራጮችና ተጠሪዎች ጋር በመሆን የግጦሽ መሬት ማሻሻያ ዘዴዎች ላይ ጥናት በማድረግ ምክረ ሃሳብ መሰጠት ይኖርበታል፡፡ |
| | 8. በአርብቶ አደሩ አከባቢ የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ግብይት ሥርዓት ለመፍጠር እና አከባቢውን በይበልጥ ለማልማትና የህዝቡንም ባህል ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት መከናወን ይኖርበታል፡፡ |
| | 9. ጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ የምርምር ውጤቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ በፌዴራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ውጤታማ ቅንጅት እንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 10. የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስን ለማስፋፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶች ወደ አምራቹ መድረስ፣ መሰራጨትና አመቺ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በልዩ ልዩ ብሔር/ ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የአህዝቦት ተግባር መከናወን ይኖርበታል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 11. የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት…) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና ሥርዓት እንዲወጣ ለማድረግ የሚያስችል ምርምር መካሄድ ይኖርበታል፡፡ |
| | 12. በኢንስቲትዩቱ በሚገኙ በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ከምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ውጤታቸውም መለካት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | 14. በኢንስቲትዩቱ የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Center) ማዕከላት ሲመረጡ ግልጽ የሆነ መስፈርት (Criteria) ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| 2. የቴክኖሎጂ_____አቅርቦት፣ ብዜትና ሥርጭት በሚፈለገው መጠን፣ ጥራቱን ጠብቆ፣ በአጭር ጊዜና አነስተኛ ወጪ ለተጠቃሚው እየቀረበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ፤ | 15. ለአርሶ አደሩ ግብርና ቅድሚያ በመስጠት ምርቱን በመጠን፣ በአይነትና በጥራት ለማሳደግ ቴክኖሎጂዎችን ለመመምርጥና ለማፍለቅ የሚያስችሉ ምርምሮች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 16. በግብርና መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮች በአብዛኛው ተግባራዊ ምርምር ላይ ያተኮሩና በአጭር ጊዜ ውጤት ሊሰጡ በሚችሉ ፕሮግራሞች ላይ ሊሆን ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 17. በአነስተኛ ወጪ ምርትን የሚያሳድጉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች እና ነባር ዝርያዎች ላይ ምርምር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 18. ከግብርና ምርምር የሚቀርቡ ቴክኖሎጂዎች ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross Cutting Issues) ያካተቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 19. የሚካሄደው የግብርና ምርምርና የሚቀርበው የግብርና ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግር የሚነሳ እንዲሁም የባለ ድርሻዎችን ስምምነት ያገኘ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 20. የቴክኖሎጂ አቅርቦት ዋነኛ መሰረት በአገሪቱ የምርምር ሥራዎች የሚገኝ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ሳይሆን ከሌሎች ሀገሮች ተመርጠው በውሰት የሚገኙ ቴክኖሎጂዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 21. በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች አገልግሎት የሚውል ቴክኖሎጂ ሊቀርብና ከእድገታቸው ጋር ተያይዞ እያደገ እንዲሄድ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 22. አርሶ አደሩ የተሟላ ፓኬጅ/ምሉዕ ቴክኖሎጂ ቀርቦለት አዋጭ የሚላቸውን ምርቶችና ሥራ ዘርፎች እንዲመርጥ ሊታገዝና ሊበረታታ ይገባል፡፡ |
| | 23. ወደ አገር ውስጥ የገባውን ቴክኖሎጂ በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት ፍተሻ ከተካሄደ በኋላ በምርምር ማዕከል ደረጃ የማላመድና የምርታማነት ብቃት ሊከናወን ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 24.ፕሮጀክቶች እና የምርምር ተግባራት በታቀደላቸው በጀት እና ጊዜ ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡ |
| 3. የምርምር ማዕከላቱ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና የግምገማ፣ የመረጃ እና የንብረት አያያዝ ሥርዓት በኢንስቲትዩቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ ማረጋገጥ፤ | 25.የአገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት አካላትን በተገቢው መንገድና ብቃት በማስተባበር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ሊጠናከር ይገባል፡፡ |
| | 26.የብዜት ተቋሞች ተለይተው የምርምር ሥርዓቱ አንድ አካል ተደርገውና ተመዝግበው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | 27.ውስን የሆነውን የአገር ኃብት (ላብራቶሪ፣ ማሰልጠኛ ማዕከል) የአገራዊ ግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት በጋራ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ |
| | 28.በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱና የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች እና መረጃዎች ማዕከላዊነት ባለው መልኩ ተሰባስበውና ተጠናቅረው በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግ አለበት፡፡ |
| | 29.የአርብቶ አደሩን የከብት ርቢ ቴክኖሎጂ ለማሻሻል በመጀመሪያ ደረጃ በአከባቢው ያለውን ልምድ በዝርዝር በመገምገም፣ ጠንካራና ደካማ ጎኑን ለይቶ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ |

| |
|---|
| 30.በምርምር ኤክስቴንሽን ገበሬ ግንኙነት መድረክ ላይ ተለይተው የታወቁትን የምርምር ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በተለየ የግብርና ኢኮኖሚክስና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ተለይተው ሊመዘገቡ ይገባል፡፡ |
| 31.የምርምር መፍትሄ ሃሳቦች የተሻሉትን ለመምረጥ የሚያስችል ተገቢው መስፈርት ማለትም የችግሮችን አንገብጋቢነት፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅምን ያገናዘበ በማውጣት ትኩረት የሚደረግባቸው የምርምር ጉዳዮች ሊመረጡና በቅደም ተከተል ተመዝግበው ሊያዙ ይገባል፡፡ |
| 32.የዕቅድ አፈጻጸሙ ሂደት በታቀደው መሰረት መሆኑንና የሚጠበቀውንም ውጤት በመጨረሻ ከማስመዝገብ አንጻር ክትትልና ግምገማ በአስፈላጊው ደረጃና ወቅት ላይ መደረግ አለበት፡፡ |
| 33.የገባውን ቴክኖሎጂ በኳራንቲን በማቆየት የጤና ክትትል ከተደረገ በኋላ ቴክኖሎጂው ከበሽታ ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡ |
| 34.ኢንስቲትዩቱ እንዲሁም የምርምር ማዕከላቱ በሩብ፣ በስድስት ወር እና በአመት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ የአፈጻጸም ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |
| 35.በኢንስቲትዩቱ የምርምር ንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

| |
|---|
| 36.በኢንስቲትዩቱ የሚፈለገውና በምርምር ሥራ የሚሰማራው የሰው ኃይል በጥናት ላይ ተመስርቶ በቅድሚያ ሊለይና በዚሁ መሰረት እንዲሟላ ሊደረግ ይገባል ፡፡ |
| 37.በግብርና ምርምር ላይ የተሰማራ ወይም የሚሰማራ ማንኛውም አካል በኢንስቲትዩቱ ተመዝግቦ በዝርዝር መያዝ አለበት፡፡ |
| 38.በግብርና መስክ የተቋቋሙትን የሙያ ማህበራት ለግብርናው ምርምር በመረጃዎች ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው ይገባል፡፡ |
| 39. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ግዥዎች ተመራማሪው/ ተጠቃሚው በሚፈልገው ወይም ባቀረበው መስፈርት(specification) እና በባለ ሙያ አስተያየት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| 40. በኢንስቲትዩቱ የተገዙ ወይም የሚገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች ወቅቱን ጠብቀው ለማዕከላት ሊቀርቡ ይገባል፡፡ |
| 41. በኢንስቲትዩቱ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው /የማይሰሩት (Expired /damaged) የሆኑት የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 42. በኢንስቲትዩቱ ስር የሚገኙ ማዕከላት በውስጥ ቁጥጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ክትትል ሊያደርጉና በአሰራር ወቅት በተለዩ ግድፈቶች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ |
| | 43. የግብርና ምርምር ማዕከላት ከተረፈ ምርት የሚያገኙትን ገቢ አሰባሰብን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ ሊያደርጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግተው ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ |


# አባሪ 2

## በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አከባቢዎች ዝርዝር ማሳያ፡-

| ተ/ቁ | የክልሉ ሥም | የፌዴራል የምርምር መዕከላት | በናሙና የተመረጡ የዞን /ወረዳ ግ/ጽ/ቤቶች | በናሙና የተመረጡ የገጠር ቀበሌዎች | በናሙና የተመረጡ አርሶ አደሮች ብዛት | በክልሉ የሚገኙ ቃለ መጠይቅ የቀረገላችወ የከፈተኛ ት/ት ተቋሚት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቤኒሽንጉል | አሶሳ የፌዴራል ግብርን ምርምር መዕከል | -አሶሳ የዞን ግ/ጽ/ቤት<br>-አሶሳ ወረዳ ግ/ጽ/ቤ/ት | -ሆሞሻ-28<br>-አንባ -14 | 10 | -የአሶሳ ዩኒቬርሲቲ እና<br>-የአሶሳ ግብርና ቴክንክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ |
| 2 | ኦሮሚያ | ባኮ የ ፌዴራል ግብርና ምርምር መዕከል | -ባኮ ወረዳ ግ/ጽ/ቤ/ት<br>-የኦሮሚያ የክልል ግብርና ምርምር ማዕከል | -ሰደን ቂጤ<br>-ቱሉ ሰንጎታ | 10 | -የባኮ ግብርና ቴክንክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ |
| 3 | ኦሮሚያ | አምቦ የፌዴራል ግብርና ምርምር መዕከል | -የአምቦ የዞን ግ/ጽ/ቤት | -ጎሱ ቆራ<br>-አማሮ | 10 | አምቦ ዩኒቨርሲቲ |
| 4 | ኦሮሚያ | ሆላታ የፌዴራል የግብርና ምርመር መዕከል | -የአምቦ የዞን ግ/ጽ/ቤት | -ጎሱ ቆራ<br>-አማሮ | 10 | -የሆለታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ |
| 5 | ሶማሌ | ፋፋን የክልል የግብርና ምርምር | -የሱማሌ ክልል | - | - | -ጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መዕከል | ግ/ጽ/ቤት<br>-የጅጅጋ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደር ምርምር ኢንስቲትዩት | | | |
| 6 | አፋር | ወረር የፌዴራል ግብርና ምርምር መዕከል | አምባራ ወረዳ ግ/ጽ/ቤት | በዱላሌ | 10 | - |
| 7 | ኦሮሚያ | ቁሉምሳ የፌዴራል ግብርና ምርምር መዕከል | ሂጦሳ ወርዳ | -አዳ ጅላ<br>-ሌሙና ቢልቢሎ<br>-ቦቆጂ ነጌሶ | 8 | አዳማ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ኮሌጅ |
| 8 | ኦሮሚያ | መልካሳ የፌዴራል ግብርና ምርምር መዕከል | - | - | 8 | - |
| 9 | ኦሮሚያ | ደብረዘይትየፌዴራል የግብርና ምርምር መዕከል | አዳአ ወረዳ ግ/ጽ/ቤት | - | - | - |

# አባሪ 3


መነሻ
ሃገራዊ የምርምር ስትራቴጂ
ወቅታዊ አንገብጋቢ ችግሮች
በምርምር ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን መለየትና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
የምርምር ፕሮጀክት ዕቅድ ማዘጋጀት
የምርምር ፕሮጀክት ዕቅድ ግምገማ (በPeer reviewing team) የሚካሄድ
ቴክኖሎጂ ማፍለቅ/ማላመድ
ስልታዊ ምርምር (Strategic Research)
አዲስ ቴክኖሎጂ ማፍለቅ/ ማሻሻል
ያለቀለት ምሉዕ ቴክኖሎጂ ማላመድ
ቴክኖሎጂ ከነሙሉ ፓኬጅ ማፍለቅ
በተጠቃሚው እጅ ያሉ ቴክኖሎጂ ከነሙሉ ፓኬጅ
ቴክኖሎጂ ማረጋገጥ፣ ማስመዝገብና መልቀቅ
የቴክኖሎጂ ቅድመ ብዜትና አቅርቦት
መጨረሻ፡- የተጠቃሚውን ፍላጎት የሚያረካ ቴክኖሎጂ ለአባዥዎችና ለግብርና ኤክስቴንሽን ማቅረብ
ግብረ መልስ
ክትትልና ግምገማ

# አባሪ-4

**በኢንስቲትዩቱ በጅት ተመድቦላቸው የምርምር ተግባራትን ሲያከናውኑ የቆዩ ተቋማት ከ1999 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም ያልተወራረዱት ገንዘብ ማሳያ ሰንጠረዥ፡-**

| ተ.ቁ | የማዕከሉ/ተቋሙ ሥም | ከ2004-2006 ዓ.ም ድረስ ያልተወራረደ ገንዘብ መጠን በብር (ጠቅላላ ድምር) |
|---|---|---|
| 1 | ጅማ የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከል | 1,747,876.56 |
| 2 | ደብረዘይት የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከል | 3,340,233.22 |
| 3 | ወረር የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከል | 9,585,526.60 |
| 4 | አረካ ግብርና ምርምር ማዕከል | 836,788.82 |
| 5 | ሆለታ የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከል | 4,563,851.92 |
| 6 | ሲሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል | 226,541.09 |
| 7 | መቀሌ ግብርና ምርምር ማዕከል | 2,876,612.70 |
| 8 | አበቦ ግብርና ምርምር ማዕከል | 113,558.37 |
| 9 | ፓዌ ግብርና ምርምር ማዕከል | 3,335,562.11 |
| 10 | አሶሳ የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከል | 1,287,121.32 |
| 11 | አምቦ የፌዴራል ግብርና ምርምር መዕከል | 315,977.38 |
| 12 | ወንዶ ገነት ግብርና ምርምር ማዕከል | 7,190,615.65 |
| 13 | ደን የፌዴራል ምርምር ማዕከል | 2,424,883.00 |
| 14 | ሰበታ ዓሣና የውኃ ውስጥ ሕይወት ምርምር ማዕከል | 663,002.69 |
| 15 | ብሄራዊ አፈር ምርምር ላብራቶሪ | 352,944.97 |
| 16 | ሰበታ እንስሳት ጤና ምርምር ማዕከል | 1,333,993.44 |
| 17 | ወንዶገነት ደን ኮሌጅ | 31,894.55 |
| 18 | አማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | 9,217,356.41 |
| 19 | የደን ውጤቶች አጠቃቀም ምርምር ማዕከል | 67846.84 |
| 20 | ባኮ የክልል ግብርና ምርምር ማዕከል | 563,563.03 |
| 21 | አዋሳ ግብርና ምርምር ማዕከል | 665,295.40 |
| 22 | ብሔራዊ እንስሳት ጤና ቬተርነሪ ኢንስቲትዩት | 137,479.31 |
| 23 | ደብረዘይት እንስሳት ጤና ሕክምና ፋካልቲ | 64,629.33 |
| 24 | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፓቶ ባዮሎጂ | 422,475.07 |
| 25 | ባሕርዳር እንስሳት ጤና ምርምር ማዕከል | 8,096.37 |
| 26 | ለኮምቦልቻ እንስሳት ጤና ምርምር ላብራቶሪ | 15,552.18 |
| 27 | አሰላ ቬተርነሪ ላብራቶሪ ምርምር | 8,627.40 |
| 28 | ወላይታ ሶዶ እንስሳት ጤና ላብራቶሪ | 49,871.38 |
| 29 | መልካሳ የፌዴራል ግብርና ምርምር መዕከል | 2,463,414.46 |
| 30 | ቁሉምሳ የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከል | 16,072,625.80 |
| 31 | አዳሚ ቱሉ ምርምር ማዕከል | 490,265.33 |
| 32 | ባኮ ብሔራዊ በቆሎ ምርምር ማዕከል | 2,411,135.36 |
| 33 | አዋሳ ብሔራዊ በቆሎ ምርምር ማዕከል | 148,376.78 |
| 34 | ሲናና ግብርና ምርምር ማዕከል | 665,981.88 |

| | | |
|---|---|---|
| 35 | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | 97,315.94 |
| 36 | ደብረብርሃን ግብርና ምርምር ማዕከል | 94,417.14 |
| 37 | አማራ ግብርና ቢሮ | 177,971.64 |
| 38 | ደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ (ፓዴፕ) | 191,821.49 |
| 39 | ሃረማያ ዩኒቨርሲቲ | 5,384,820.56 |
| 40 | አዋሳ ግብርና ኮሌጅ/ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ/ | 395,927.52 |
| 41 | ጅማ ግብርና ኮሌጅ/ጅማ ዩኒቨርሲቲ/ | 207,258.07 |
| 42 | አምቦ ግብርና ኮሌጅ/አምቦ ዩኒቨርሲቲ/ | 96,596.48 |
| 43 | ዝዋይ ዓሣ ግብርና ምርምር ማዕከል | 8,739.50 |
| 44 | ኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | 11,479,753.36 |
| 45 | ሆለታ ንብ ምርምር ማዕከል | 2,724,777.98 |
| 46 | ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ | 33,000 |
| 47 | ሱማሌ ክልል የእንስሳት እርባታና ከፊል እርሻ ምርምር ተቋም | 4,438,736.25 |
| 48 | ጂንካ ምርምር ማዕከል | 1,508 |
| 49 | በደሌ እንስሳት ጤና ላብራቶሪ | 13,222 |
| 50 | ቦንጋ ግብርና ምርምር ማዕከል | 2,175.47 |
| 51 | ሰመራ ግብርና ምርምር ማዕከል | 309,618.37 |
| 52 | ሁመራ ግብርና ምርምር ማዕከል | 149,084.33 |
| 53 | አክሱም ግብርና ምርምር ማዕከል | 78,957.82 |
| 54 | ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል | 13,901.55 |
| 55 | አፋር አርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ምርምር ኢንስቲትዩት | 274,943.34 |
| 56 | ጋምቤላ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | 22,127.08 |
| 57 | ደቡብ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | 3,391,385.20 |
| 58 | ትግራያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | 2,130,994.04 |
| 59 | ጎንደር ዩኒቨርሲቲ | 60,000 |
| 60 | ቴፒ ብሔራዊ ቅመማ ቅመም ምርምር ማዕከል | 115,390.19 |
| 61 | ወሎ ዩኒቨርሲቲ | 8,926 |
| 62 | ሸራሮ ግብርና ምርምር ማዕከል | 9801 |
| 63 | አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ | 28,003 |
| 64 | ፎገራ ግብርና ምርምር ማዕከል | 83,581 |
| 65 | ምሆኒ ግብርና ምርምር ማዕከል | 2,997,910.27 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **108,722,241.00** |